# ትግላችን

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

( አ.አ.ኢ.ተ.ፌ. አባል )

ስለ ሕዝባዊ ድርጅቶችና
የተማሪው ድርጅት
ተግባር

የካቲት 1973 ዓ.ም.

# መግቢያ

በጥናትና በምርምር ላይ የተመሠረተ ትግል ሕያውነት አለው:: በዚህ መሠረታዊ ኃባብ ላይ የተቋቋመ ድርጅት ዘላቂነት ያለውና ብዙኃንን አባላት ሊያቅፍ እንደሚችል የብዙኃኖች የትግል ታሪክ መስክሯል:: በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር /ዓ.ዓ.ኢ.ተ.ፌ.አ/ ይህን ታሪካዊ ጠቀ በመገንዘብ በትግል መስክ ከተመሰረተበት ወቀት አንስቶ የተማሪው ማሕበር ተከከለኛውን መድረክ እንዲቀዳጅ፣ በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብይ ጠላቶች ላይ በመቃወም፣ ከመሳይ ሕዝባዊ ድርጅቶች ጋር እንዲተባበር ወ.ዘ.ተ ለማድረግ የማያቋርጥ ትግል አድርጓል፣ ወደፊትም ማድረግ ይኖርበታል::

አንድ ድርጅት በትግል ወላፈን ውስጥ ከገባበት ወቀት አንስቶ ውጣ ውረዶች እንደሚያጋጥሙት የታወቀ ነው:: የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ከዚህ ነባራዊ ጠቀ ሊርቀ አይችልም:: ዋናው መተኮር ያለበት ነጥብ ግን እነዚህን ውጣ ውረዶች አውቆ መፍትሄአቸውን በወቀቱ በመሻት በተከከለኛ ጎዳና በትጋት መጓዝ ነው:: ስለሆነም በአውሮፓ የኢ.ተ. ማሕበር /ዓ.ዓ.የኢ.ተ.ፌ አባል/ ለችግሩ መውጫ ይሆኑት ዘንድ በየአመቱ የተለያዩ ጥናቶችን ሲያካሄዱ ቆይቷል:: በዚህም መሠረት በአለፈው የ20ኛው አመታዊ ጉባኤ ጥናት እንዲካሄድ ውሳኔ አስተላለፏል:: በውሳኔውም መሠረት ከተላለፉት የጥናት ዝርዝሮች መካከል ለጊዜያዊ ችግሮቻችን መፍትሄ ይጠቅማሉ በሚል ዕምነት ከስዊድን ቅ/ማኅበር ጓዶች ስለሕዝባዊ ድርጅቶች አጭር የፅንስ ሐሳብ /ቲዎሪ/ መንደርደሪያ ለጥናትና ለክርክር አቀርቧል:: ይህም ርዕስ በሚከተሉት ንዑስ ክፍሎች ተከፋፍለዋል::

ሀ. ሕዝባዊ ድርጅት ምን እንደሆነ?

ለ. የሕዝቦች የመደራጀት አላማ ለምን እንደሚያስፈልግ፣

ሐ. በሕዝባዊ ድርጅቶች መካከል የሚኖረው ልዩነትና

እንድነት፣

መ. የሕዝባዊ ድርጅቶች ሚና በልዩ ልዩ ወቅቶች

ሠ. በድርጅቶቹ ውስጥ የፖለቲካና የርዕዮተ ዓለም ጥያቄዎች እንዴት ይንሸራሸራሉ?

ረ. በተለይም የተማሪው ክፍል ከቀረው የሕብረተሰብ ክፍሎች በምን እንደሚመሳሰልና እንደሚለያይ

ሰ. የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በአሁኑ ጊዜ የትግል መርሆው ምን መሆን አለበት?

ሕዝባዊ ድርጅት ራሱን የቻለ ሰፊና በጣም የሚያወያይ ርዕስ ነው:: ስለሆነም ማንኛችንም በዚህ ርዕስ ላይ የምንችለውን ያህል ሐሳብ ከመሰንዘር ወደኋላ ማለት እንደሌለብን አስቀድመን ለመጠቆም እንወዳለን::

ከዚሁ ጽሑፍ ጋር በተጨማሪ ስለ 1966 ዓ.ም የየካቲት ሕዝባዊ ንቅናቄን ምክንያት በማድረግ አንድ የመታሰቢያ ጽሑፍ ቀርቧል::

## ክፍል 1. ስለሕዝባዊ ድርጅቶች

የመጀመሪያው ክፍል በይበልጥ ያተኮረው ስለሕዝባዊ ድርጅቶች ትርጓሜ፣ ስለድርጅት አስፈላጊነት፣ ስለድርጅቶች ሚናና በሕዝባዊ ንቅናቄ ወቅቶች የድርጅቶችም ተሳትፎና ሚናን የሚመለከት ነው::

በርግጥ "ብዙሃን" የሚለውን ቃል በሚገባ ለማብጠርጠር አንድን የተወሰነ ህብረተሰብ በማንሳት የመደብ ትንተናዎችን በመስጠት፣ የመደቦችን አሰላለፍ፣ የስልተምርቱን አስረጧጧትና አደረጃጀት በማስተንተን ብዙሐኑን ከጥቂቱ፣ የጥቂቱን ጥቅምና የብዙሐኑን ጥቅም በመለየት ባይንቷፊክ መልስ ማቅረብ ተገቢ ነውን ይህን ጥያቄ በዚህ ደረጃ ለማቅረብ በአሁኑ ወቅት አቅማችን ባይፈቅድልንም፣ ይህን ትንታኔ ባለማቅረብ በቀላሉ የሕዝባዊ ድርጅቶችን ምንነት ከህብረተሰብ በተገኙ ልምዶችና ከሚታዩ ሁኔታዎች በመነሳት ለሰፊ ውይይት ማቅረብ እንሞክራለን::

"ብዙሐን" የሚለው ቃል በጅምላ አገላለጽ ከአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ካሉት የሕብረተሰቡ አባላት መካከል በህብረተሰቡ ውስጥ የተፈጠሩትን የፖለቲካ፣ የምጣኔ ሀብትና የባሕል ችግሮች ተሸካሚዎች የሆኑት ወገኖች ናቸው:: ይህም ማለት በአንድ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅትና በተወሰነ ስልተ ምርት ደረጃ የሚገኝ በዚሁ የተወሰነ ስልተ ምርት መሠረት ሰዎች ከማፍሪያ ሀብቶች ጋር ባላቸው ዝምድና ከራሳቸው ህልውና ነፃ በሆነ መንገድ በሚገቡበት ግንኙነትና በተጨማሪም በህብረተሰቡ የምርት አስረጧጧት ዘዴ አማካይነት የተለያዩ ጥቅሞችን የሚያንፀባርቁ በህብረተሰቡ ውስጥ ብዙሀን በመባል የሚታወቁ ይኖራሉ:: እነዚህ በብዙሐንነታቸው የሚጠሩት የህብረተሰቡ ክፍሎች ብዙ የወል ጥቅሞች የጋርዮሽ የሆኑ አሏቸው:: በመተባበርም ወይም ህብረትን በጋራ በማድረግ ድርጅትም በሚፈጥሩበት ጊዜ የጋራ ፍላጐታቸው፣ ጥቅማቸው በድርጅት የሚተሳሰሩበት ማዕከላዊ ነጥብ ነው::

በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በብዙ መንገዱ ይለያያሉ። በትምህርት፣ በሥራ፣ በዘር በሃይማኖት፣ በቋንቋ በባህልና በፆታ፣ በገቢ መጠን ወ.ዘ.ተ ይለያያሉ። ይሁን እንጂ በሰዎች መካከል ካለው ወይም ሊኖር ከሚችለው ልዩነት ሁሉ ዓይነተኛውና ዋናው ልዩነት የመደብ ልዩነት ነው። ከዚህ ነው ሊገጣጠሙ ወይም ሊታረቁ የማይችሉ የህብረተሰብ ጥቅሞች የሚመነጩት፤ "ሕዝባዊ" የሚለውንም በፆታ፣ በሃይማኖት በመሳሰሉት ብቻ መከፋፈሉ ጠባባዊነት ይሆናል። የህብረተሰብ ዕድገት፣ እንቅስቃሴ የሚመነጨውና የሚመራውም ህብረተሰቡ በተገነባበትና ምንጩ በሆነው ስለተ ምርት ስለሆነ፣ ከዚህ የሚመነጨው ሁኔታ ነው የህብረተሰብን አባላት 'ብዙሐን' 'ጥቂቶች' ብሎ ትንታኔ ማድረግ የሚቻለው።

ብዙሐኑ የህብረተሰቡ መሠረት ከሆኑት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ሶሻላዊ ግንኙነቶች አንፃር የጋራ ወይም የወል ጥቅሞች ካሉትና በገሃም ሆነ በነጠላ ከነዚህ ከሚመነጭ ቅራኔ በደል የሚደርስበት ከሆነ በድርጅት የጋራ ዓላማቸውን ለመስራት ይነሳሉ። 'ድርጅት' የሚለውም ቃል የመተባበሪያ፣ የመዋሃጃ ትርጉም ያለው ሲሆን፣ 'የብዙሐን ድርጅቶች' የሚለውም ጸንሰ ሐሳብ በብዙሃኑ የህብረተሰቡ ክፍል የጋራ ጥቅሞቹን በተባበረ ሃይል ለማሻሻል፣ የጋራ ጥቅሞቹን ከግቡ ለማድረስ፣ የጋራ ችግሮቹን በመተባበር ለማስወገድ የሚደራጅበት ድርጅት ነው።

ሰዎች በመደብ ከተከፋፈሉበት ዘመን ጀምረው ለመግዛት ወይም ላለመግዛት፣ በተከከለኛው የሰልጣኔ ጎዳና ለመጓዝ ወይም ላለመጓዝ በአደረጉትና በሚያደርጉት ዝሻሚያ ብዙ ትምህርትን አግኝተው ለሚተኩቸው ተውልዱ ቅርስን አስቀምጠው እንዲያልፉ ሆነዋል። ባሕል፣ ሥልጣኔና ሐብት የሠራተኛው ሕዝብ ሆኖ ባለጥቂቶች በዝባዦች እንደፈለጋቸው ሲያዙበትና ሲደሰቱበት፣ የተመለከተና የጭቁን ቀንበር መሸከሙ የመረረው ትግሉን እንዴት እንደሚመራው በቅጡ ማሰብ ግዴታው ነበረ። ጭቁን አንድ አይነት አይደለም፣ በፍፁም ሊሆንም አይችልም። የበዝባዥ መደብ የጭቁ



ና አውታሩን ለማስፋፋት በየአቅጣጫው መጓጠጥ፣ ጭቁኖችን ማበጣበጥ፣ አንዱን ክፍል በሌላው ላይ ማዝመት፣ አንዱን ከሌላው አብልጦ የወደደ አስመስሎ ማቅረብና እስከ መጠቀሚያ ማድረግ የመሳሰሉትን አስከፊ ድርጊቶችን ይፈጽማል። ጭቁና ደግሞ እንደ ዘመኑ እንደ ሃገሩ፣ እንደሁኔታው ይለያያል፣ እጥፍ ድርብም ይሆናል። ለዚህ ነው የሕዝቦች ጭቁና የተለያየ የሚሆነው፣ ስፋትና ጥልቀትም የሚኖረው። እንግዲህ እንደዚህ በተለያየ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የጭቁና ወጥመዶች የተተበተቡ ሕዝቦች ከዚህ የገፈፋ ሁኔታ ለመውጣት ምን ማድረግ አለባቸው? መራራ ኑሮ ያንገዳገዳቸው ሕዝቦች በተሰበጠረ የግላዊ ትግል ሁኔታ አጥጋቢ ውጤት ለማግኘት እንደማይችሉ የራሳቸው ታሪክ አስተምሮአቸዋል። ስለሆነም ሕዝቦች በመደባቸው በተዋረዱ እንዲሰለፉ፣ በድርብ የፆታ እስር ቤታቸውና በማኅበራዊ ኑሮአቸው፣ በሥራቸው ወ.ዘ.ተ አንፃር እንዲሰባሰቡ ምክንያት ይሆናቸዋል። በእነዚህ ከላይ በተዘረዘሩት ቅራኔዎችና በአንፃሩም ቅራኔዎችን ለመፍታት በሚደረገው መሰባሰብ በዘመኑና በእያንዳንዱ ሀገር አብይ ቅራኔዎች ላይ የተመሠረተ ይሆናል። ከዚህም የተነሳ አንዳንዶቹ ቅራኔዎች ከሌሎች ከበደው ይታያሉ፣ ግንባር ቀደምም ሆነው ይቀርባሉ። ለምሳሌ የከበርቴ ሥነሥርዓት ለመስፈን በአንጸበበበት ጊዜ ዋና ቅራኔው የነበረው 'የነፃ ውድድርን' በሚያራምደው በዘመኑም ለተወሰነ ጊዜ በምጣኔ ሀብት ሆነ በሰልጣኔ ባሕል ተራማጅ አስተሳሰብ በነበረው በከበርቴውና በመሬት ሥሪት ላይ አይኑን በተከለው በፊውዳሊዝም መካከል ነበረ። በእዚህ ቅራኔ ላይ የተሰለፈው ከበርቴው ብቻ ሳይሆን በማደግ ላይ የነበረውም ላብ አደሩ፣ ለዘመናት ሲወርዱ ሲዋረዱ በመሬት ሥሪት አለንጋ ሲገረፍ የነበረው ገበሬው፣ ንዑስ ከበርቴውና ሌሎችም ጭቁን የሕብረተሰብ ክፍሎች የራሳቸውን ጥያቄ ከዋናው ጥያቄ ጋር በማቀናጀት የተሰለፉ መደባትም ነበሩ።

የኢምፔሪያሊዝም ዘመን ደግሞ የረቀቀ ዋብዝበዛ ሥነ ሥርዓት አስከተለ። ይህም ዘመን በከበርቴውና በላብ አደሩ መደብ ገብገብ፣ የኢምፔሪያሊስቶች /የሶሻል ኢምፔሪያሊስቶች/ የእርስ በርስ ጕሽሚያ፣ በኢምፔሪያሊስት አገሮችና በቅኝ ግዛት አገሮች መካከል ፍልሚያ፣ በኢምፔሪያሊዝምና በሶሻሊዝም አብይ ቅራኔዎች የተሞላ ነው። ስለሆነም የተጨቆኑ ሕዝቦች ከተለያዩ የጭቆና አይነቶች ነፃ ለመውጣት ትግላቸውን የሚያጧጡፉበት ዘመን ነው።

በአጭሩ ሕዝባዊ ድርጅቶች ችግራቸውን በሰፊው የሚወያዩበት፣ ሀሳባቸውን ተግባራቸውንና ትግላቸውን የሚያቀነባብሩበት ሲሆን ከዘመኑና ከእያንዳንዱ ሀገር ቅራኔዎች ላይ በመመሥረት የሚወጣ ብሎም የሚያድግ የመታገያ መሣሪያ ነው። ይህም መሳሪያ /ድርጅት/ በተወሰነ መድረክ ላይ ይመሠረታል። መድረኩም ሰዎች ለተወሰነ ዓላማ ለጋራ ጥቅም በተቀነባበረ ሁኔታ ክንዳቸውን በጠላት ላይ እንዲያነሱ የሚያስችላቸው ማዕከላዊ መመሪያ ነው። ይህ ማዕከላዊ መመሪያ መድረክ በስፋት ሆነ በጥልቀት አንፃር ሲታይ በተለያዩ ሐገሮች ወይም በአንድ ሃገር ውስጥ የተለያየ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም በመድረኩ ውስጥ የሚጠቃለሉት የቅራኔዎች ብዛትና ብስለት በተለያየ ደረጃና ቀደም ተከታይነት ሊኖራቸው ይችላሉና!

ለዚህ ነው የተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚያጠቃልለው መድረክ በተለያዩ ሐገሮች የሚገኙትን ተጨቋኝ መደቦችን ይቀርና በአንድ በተወሰነ ሐገር ውስጥ የሚገኙትን ምዝበር ሕዝቦችን እንኳ የሚወክለው መድረክ ሊለያይ የሚችለው። እርግጥ መድረክ ከመደብ ንቃት፣ ከባህልና ከምጣኔ ሀብት ዕድገት ጋር ብሎም ከአብዮታዊው ትግል ውጣ ውረድ ጋር ተያይዞ የሚሄድ ነው። ስለሆነም ሕዝባዊ ድርጅት በሰላማዊ ወቅት ሆነ በአብዮታዊ፣ በጨለማ ዘመን ሆነ በተረጋጋ ወቅት የሚፈጠሩ ፖለቲካዊና ድርጅታዊው ጥንካሬው ሆነ ርዕዮት አለማዊው ብስለቱ የሚለያይ



ሲሆን ሕዝቦች ለከፍተኛ ትግል በሁሉ አንፃር የሚዘጋጁበት ትምህርት ቤታቸው ነው። ስለሆነም ሕዝባዊ ድርጅት በአንዱ ቦታ ላ የአረፈ የማይንቀሳቀስ /static/ የማይለወጥ በድን /fossified/ ሳይሆን ከአፖለቲካል /non-political/ ደረጃ ተነስቶ ትልቅ የፖለቲካ ግፊት ሊሆን የሚችል፣ ከጥቂት ግለሰቦች ተነስቶ መላ ሕዝቦችን ለማቀፍ የሚችል፣ በትግል አለም ሳለ ውጣ ውረዶችን እየተጋፈጠ በትግል የሚሰማራ ነው።

እንግዲህ ሕዝባዊ ድርጅት ምን እንደሆነ ከተረዳን ሕዝቦች ለምን በፈርጁ በፈርጃቸው የሚደራጁበት አላማ ምን እንደሆነ እንመልከት። የሰው ልጅ የትግል ታሪክ እንዳሳየን በከፊል ጥቂትና 'የመነጠቁ' ሰዎች ብቻ የሕብረተሰብን ጥያቄ አንስተው እስከመጨረሻ ገፍተው ትክክለኛ መፍትሄ ሊያስገኙ አይችሉም። ምንም እንኳን እነዚህ ጥቂት ተራማጅ የሀብረተሰብ ክፍሎች የሕብረተሰቡን አብይ ጥያቄ አጢነው ቢያውቁትም በተግባር ላይ ግን የሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ ከሌለበት ግቡን እንደማይመታ መገንዘብ ይኖርባቸዋል። ታዲያ የሕዝቦች ተሳትፎ በአንዴት አይነት መንገዱ መቀነባበር አለበት? ትግል በግብታ /spontaneous/ የተመራ ከሆነ ብዙ ጊዜ ሳይቆይ ለጠላት የሚንበረከክና በቀላሉ የሚፈረካከስ ይሆናል። ይህም ጊዜያዊ ውድቀት ለተወሰነ ጊዜ እንኳን ቢሆን የጠላትን ኃይል ያጠናክራል። ስለዚህ ሕዝቦች ትግላቸውን የሚያቀነባብርላቸው አካል ማለት ድርጅት ተቀዳሚ ስፍራን ይይዛል ማለት ነው። በእርግጥ ድርጅት በቀላሉ የሚፈጠር ነገር አይደለም። ይህም የራሱ የሆነ ምክንያት አለው።

በተቀዳሚ ነገር ድርጅት የተወሰኑ ሰዎችን ፍላጎትና ጥቅም የሚጠብቅ፣ ኃይላቸውንና አቋማቸውን የሚያስተጋባ እንደመሆኑ መጠን ሰዎች እርስ በርሳቸው በኅሳብም ሆነ በጋራ በትግል ሰንሰለት እስከሚተሳሰሩ ዕለት ድረስ ረዝም ያለ ጊዜን የሚፈጅ ሂደት ነው። በዕውነትም የሚፈጠረው ድርጅት ጠንካራ እንዲሆን ከተፈለገ ችግሩ በይበልጥ የተሰማቸው ግለሰቦች የማያቋርጥ ቀስ

ቀሳ ማድረግ ታሪካዊ ግዴታቸው ነው፡፡ የቀስቃሹም ዓላማ ሕዝቦች እርስ በርሳቸው በጋራ ቸግራቸው እንዲቀራረቡ ብሎም የመታገያ ድርጅታቸውን በትክክለኛው መንገድ እንዲመሠረቱ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ ህዝቦች በትክክለኛው መንገድ ከተደራጁ ድርጅታቸው የተነሱበትን አላማ ከግቡ ሊያደርስላቸው ይችላል፡፡

ስለሆነም የመደራጀትና የማደራጀት አላማ አጭርና ረጅም ገብ ይኖረዋል፡፡ ለምሳሌ ድርጅት አንደኛውና ዋናው አስፈላጊነቱ የሕዝቦች አላማ ትክክለኛ መስመር እንዲከተል ማድረግ ቢሆን አባላት ከዕለታዊ ተግባራቸው የበለጠ ተምረው በላቀ አኳኋን ድርጅታዊ ፍላጐታቸው እንዲሟላላቸው ቢጥርም ጭምር ነው፡፡ ድርጅታዊ ፍላጐት ማለትም በአንድ በተወሰነ ድርጅት ውስጥ የሚገኙት አባላት ትግል ተሰሚነትና ዘላቂነት እንዲኖረው ለትግሉ አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን ትክክለኛ የፖለቲካ፣ የርዕዮተዓለም የባህልና የሶሻል ትምህርቶች በተገቢው መንገድ በድርጅቱ አባላት ውስጥ እንዲስፋፉ ማድረግ፣ ትግሉ ከአነስተኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ቀስ በቀስ እየጋየ እንዲሄድ ለማድረግ ከፍተኛ ምርምርንና እርምጃን ለመውሰድ ቢጥር፣ በአጭሩ የድርጅታዊው መርሆው በአነስተኛውና በከፍተኛዉ የሕዝቦች ትግል በደንብ የተጠመሩ መሆናቸውን ዋስትና ቢሰጥ ማለት ነው፡፡ የሕዝቦች አርነት የሚመጣው ትግላቸው ከዝቅተኛነት ወደከፍተኛነት ደረጃ ቢሄድ ከሰላማዊነት ወደአመፅ ቢራመድ፣ ከበትንትንነት ወደ ቀንበብርነት ቢያመራ በአጭሩ ትግላቸው እንደብረት ሰንሰለት የተያያዘ ቢሆንላቸው ብቻ መሆኑ ዕሙን ነው፡፡

በእርግጥም አንድ ድርጅት በትግል መብሰሉ የሚመዘነው የአባላቱን የንቃት ሕሊና መርምሮ የተረዳ ከሆነና ትግላቸውንም በአላቸው ደረጃ ከአካሄዳቸውም ጭምር ነው፡፡ እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ጠቆች ከግብ ለማድረስ፣ በምጣኔ ሀብት ሆነ በፖለቲካ በባሕል ሆነ በሌላም ረገድ አፍኖ የያዛቸውን የጨቋኝ ወገን ለመታገል ብሎም ገርስሶ ለመጣል ምዝብሮችን ያስችል ዘንድ ነው የድርጅት አስፈላጊነቱ!!



ቀደም ቢል እንደተገለጸው የጨቋኝ ወገንን ለመደራደርም ሆነ ከስሩ ነቅሎ ለመጣል ሕዝቦች በግዴታ ከስብጥርጥርነት ይልቅስ የተቀናጀ ትግል በየድርጅታቸው አማካይነት አስተዋጽኦ ማድረግ እንዳለባቸው ከራሳቸው መራራና ጠምዛዛ የትግል ታሪክ እንደተማሩ አይተናል፡፡ በተጨማሪም በአንድ በዘባጅ ሥነ ሥርዓት ውስጥ የተለያዩ የጭቆና ቀንበሮች እንዳሉና በአንፃሩም የተለያዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች እንደአሸን ሊፈሉ እንደሚችሉም በመጠኑም ቢሆን ተመልክተናል፡፡ የተቀነባበረና ብሔራዊ አቀፍ ትግል እንዲካሄድ ከተፈለገ የእነዚህን እንደአሸን የፈሉትን ድርጅቶች ልዩነቶችና ግንኙነቶች ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ የኢምፔሪያሊዝም ሥነ ሥርዓት በሰፈነባቸው ሀገሮች የአሉት ሕዝባዊ ድርጅቶች በከፊል ፊውዳል ከፊል የከበርቴ ሥነ ሥርዓት ሥር ከሚገኙት ሕዝባዊ ድርጅቶች የመታገያ መድረካቸውና አጠቃላይ ትግላቸው በእያንዳንዱ ሀገር አብዩ ቅራኔያቸ የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠን የመታገያ መድረካቸው ለየት ያለ ነው፡፡ የሶሻል ኢምፔሪያሊዝም የሰፈነባቸው አገሮች ሕዝቦች ለመደራጀት የሚፈልጉበት ከዚያም የእርስ በርስ ትግላቸውን የሚያቀነባብሩበት መንገድ የተለየ ነው፡፡ በተመሳሳዩም ቢሆን እንኳን በተለያየ ሥነ ሥርዓት ያሉትን ሕዝባዊ ድርጅቶች ይቀርና በአንድ በተወሰነ ሀገር ያሉትንም ድርጅቶች አንድ አይነት መልክ ለመስጠት ወይም ለችግራቸው አንዱ ወጥ መፍትሄ ለመሻት መሞከር የሕዝቦችን ትግል ማፈራረስ ይሆናል፡፡

በተለይ የአብዮት ወላፈን በአለበት ወቅት ሁሉን ድርጅቶች ከፍ ባለ የዕኩል ደረጃ እንዲሳተፉ መመኘት ወይም የጠላት ኃይል አይሎ ትግሉ ቀዝ ቀዝ በሚልበት ወቅት ሁሉንም ድርጅቶች ዝቅ አድርጎ ማንቋሰስ ሕዝባዊ ድርጅቶቹ ከነአካቴው ከትግል መድረክ እንዲጠፉ የሚያስችል አደጋ ሊኖር ይችላል፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱን ድርጅት ይዞ ከተነሳበት መፈክርና ከድርጅታዊ ጥንካሬውም አንፃር ብቻ ነው በአብዮቱ ውስጥ መሳተፍ የሚኖርበት፡፡

ቀጥሎ በሌላ ወገን የሚመጠው ፅንሰ ሐሳብ ደግሞ እያንዳንዱ ድርጅት የራሱን ጥያቄ ከሌሎቹ የሕዝባዊ ድርጅቶች በተናጠል ይዞ ቢታገል ቀስትና ያለው መፍትሄ ሊያገኝ ይችላል ወይ? ቀደም ተደርጐ ለመጠቆም እንደተሞከረው ምንም እንኳን በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ የተለያዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች የተለያየ የመታገያ መድረክ ይዘው ቢቀርቡም ቀሉ አንዱ አማካይ ነጥብ ሁሉን ያስተሳስራቸዋል:: ይኸውም ነጥብ የጋራ የመደብ ጠላት በመኖሩ መሆኑ ግልፅ ነው::

ሕዝቦች ይህ የጋራ ጠላታቸው ችግራቸውን በተናጠል ሸንግሎ ለማለፍ አለበለዚያም ጀርዳባ ልበስ እንደሚላቸው ከአጋጠመውም የአመፅ ድምፃቸውን ለማጤናገፍ ጊዜና ቦታ እንደማይወስነው ከብዙ አብዮታዊ ውድቀቶች ታሪክ ተምረዋል:: ስለዚህ ድርጅቶች ምንም እንኳን በመድረክ የተለያዩ ቢሆኑም የግል መድረካቸው ግብ እንዲመታ ከተፈለገ በግድ ትግላቸው የተቀነባበረ ዋና ጠላትን በአንድ ላይ ወደመጣሉ ያመራ መሆን አለበት:: በማንኛውም አንፃር ከተወሰደ የአንዱ ድርጅት ፍላጐት መሟላትና አጠቃላይ ሕይወቱ መጎከቱ በሌላው ሕዝባዊ ድርጅት ጠንካራና የተሳካ ትግል ጋር የተሳሰረና የተጣመረ ይሆናል:: ከዚያም አልፎ የትግል ስልት፣ መልካም አብዮታዊ ትምህርት አንዱ ከሌላው ሊማርና በአብዮታዊው ትግል ውስጥ በሙሉ ልብ እንዲካፈል ያደርገዋል:: ከመድረኩም ላቀ ያለውን መጠይቅ አንስቶ በጠላት ላይ ከንዳን እንዲያነሳ ያደርገዋል:: በእንደዚህ አይነት ረገድ የተገናኙ ሕዝባዊ ድርጅቶች ዘለቄታዊ የትግል አጋርነት እንዲኖራቸውና አላማቸው እንዲሳካላቸው ያስችላቸዋል:: ስለዚህ በሕዝባዊ ድርጅቶች መካከል ሊኖር የሚገባውን ልዩነትና ተመሳሳይነት በቅጡ ማጤን ሕዝቦች የተነሱበትን አላማ ከግቡ ለማድረስ ይረዳል::

የከበርቴው ሥርዓት በገነነባቸው አገሮች የሕዝባዊ ድርጅቶች ሚና በልዩ ልዩ ወቅትና የሕብረተሰብ ሥነ ሥርዓቶች በጣም የተለየ ነው:: የገዥው መደብ በፖሊስና በጓንዳርሚው ታጅ



ቦ እግሩን አንፈራጦ ማን አለብኝ ብሎ "የሰላም ድርድርን" ሲወርጥ ሕዝባዊ ድርጅቶች የኢኮኖሚና የፖለቲካ ትግላቸውን በሕጋዊ /legal/ መንገድ የሚያጧጡፉበት ጊዜ ነው:: ይህ ወቅት በአብዮታዊው ወገንና በፀረ አብዮት ወገን የኃይል ሚዛኑ "ወይ መመጣጠኑ" በደረሰበት አካባቢ ይሆናል:: ነገር ግን የጨለማ ወቅት ሲመጣ /reign of reaction § terror/ ሕዝባዊ ድርጅቶች አቅማቸውን በመመዘን ጉልበታቸውንና ድርጅታዊ አንድነታቸውን ከጠላት ኃይል ለመጠበቅ ወደኋላ የሚያሸገሽጉበትና በሚስጢር ተግባራቸውን የሚያካሂዱበት ጊዜ ይሆናል:: የጭቁኖች ሃይል አይሎ የገዥው መደብ በድሮው አይነት መንገድ ለመግዛት ሲያቅተውና ሕዝቡም አሻፈረኝ አልገዛም ብሎ ለአዲስ ሥርዓት አጠ ከመጨረሻ ደምጠብታው በሚዋጋበት ወቅት መላ የተጨቆኑ ሕዝቦች በድርጅታቸው አቀነባባሪነት ትግላቸውን ከመሰል ታጋዮች ጋር አንዲያስተባብሩ ይሆናሉ::

ኒዮ ኮሎኒያል በሆነ አገሮች የዲሞክራሲ ጭላንጭል በማይታይባቸው ሕዝቦች የራሳቸውን ድርጅት ለመፍጠር የማይፈቀድበት አገዛዝ ውስጥ ለይስሙላ ያለው መንግሥት በራሱ አምሳያ በሚጠቀምባቸው ዘዴ እንዲደራጁ መመሪያ ለጋሽ ሆኖ ይቀርባል:: የሚፈጠሩትም ድርጅቶች እንደየሁኔታው ትግላቸውን በጋራ ጠላቶቻቸው, ላይ ለማሳረፍና አዲስ የትግል ምዕራፍ ለመክፈት ይታገላሉ:: በአብዮታዊ ንቅናቄዎች ወቅት የሕዝባዊ ድርጅቶች የሚታገሉላቸው ጥያቄዎች በከፍተኛ ደረጃ የአርነት መውጫ ጐዳናው በርዕዮተዓለም መነፅሩ በሚመለከተው በላባአደሩና በአጋሮቹ ፓርቲ አማካይነት ትክክለኛ አመራርን ይይዛል::

የሰፊው ሕዝብም አብዮታዊ ንቅናቄ በድል ካከተመ እነዚህ ሕዝባዊ ድርጅቶች በሶሻሊስት ግንባታ በንቃት መሳተፍ፣ የጭቁኖችን አምባገነናዊ የበላይነት መቀበልን፣ የፓርቲውን አመራር መቀበል፣ አብዮትን መከላከል፣ አብዮታዊ ተመክሮዎችን መማርና ማስተማርን ከፓርቲው ጋር የጋራ ተግባርና አላማ ሚነደፍ

ባቸው ነጥቦች ይሆናሉ።

ክፍል 2. በዚህ ክፍል ለማቅረብ የምንሞክረው በሕዝባዊ ዴር
ጅቶች ውስጥ የፖለቲካ ጥያቄና የርዕዮተ ዓለም አ
መለካከቶች ያሏቸውን ሥፍራ፣ ስለተማሪው ክፍል ም
ንነትና የተማሪው ዴርጅት ተግባር ምን መሆን እን
ዳለበት የሚገልጽ ነው።

በቀዳሚያ በፖለቲካና በርዕዮተ ዓለም መካከል ያሉትን
ልዩነቶች ወይም ቀንጆቶች ለማግለጽ እንሞክራለን።

ርዕዮተዓለም በቀላል አነጋገር በአንዱ መደብ ጥቅምና ፍ
ላጐት ላይ ተመስርቶ ስለማህበራዊ ኑሮ፣ ስለፖለቲካ፣ ስለምጣኔ
ሃብት የሚስነዝር ሐሳብ ነው። ርዕዮተ ዓለም የዕምነትና የአ
ስተሳሰብን ይዘት ያጠቃልላል። ለምሳሌ የፖለቲካ፣ የሕግ፣ የ
ሥነ ሥርዓት፣ የሃይማኖት፣ የፍልስፍና ወ.ዘ.ተ ርዕዮተ ዓለ
ም በአንዱ ሕብረተሰብ የምጣኔ ሃብት ላይ የተመሠረተ የላዕላይ
መዋቅር ነው። ስለሆነም የምጣኔ ሐብት ግንኙነትን ያንፀባርቃ
ል። ካፒታሊዝም በታሪክ መድረክ ላይ ብቅ ካለበት ወቅት እን
ስቶ በዓለም ውስጥ ሁለት ዓይነት ርዕዮተ ዓለሞች ይገኛሉ።
እነዚህም የከበርቴውና የላብአደሩ ርዕዮተ ዓለሞች ናቸው። እ
ነዚህም ርዕዮተዓለሞች መደባዊ ፀባይ ስላላቸው ለመደባቸው የ
መደብ ጥቅምን በተቻለ መጠን በከፍተኛ ደረጃ የማስጠበቂያ ስት
ራተጂና ታክቲክስን ያዘሉ ናቸው። የላብአደሩ ርዕዮተ ዓለም
የሚለይበት ግን የሕብረተሰብ እድገትን የተከተለ ሳይንሳዊ ርዕ
ዮተዓለም ነው፣ ስለዚህም ለሰላም፣ ለነፃነት፣ ለዕድገት የሚጥ
ሩትን ሠራተኞውን መደብና የሰፊውን ህዝብ ፍላጐት የሚያስተጋ
ባ ነው። ይህም በከፍተኛ ደረጃ ማለት የመደቦች ተወካዮች አ
ማካይነት ዴርጅታዊ ቅርጽ በመያዝ ይንፀባረቃል።

በሌላው በኩል ደግሞ ፖለቲካ የርዕዮተዓለም ተርጓሚ
አንዱ ክፍል ነው። የመንግሥትን ዓይነት፣ አቋሙን ለመግለጫ



የሚውል ሲሆን፣ በተጨማሪ ፖለቲካ ለብቻው የተነጠለ ሳይሆን
ከህብረተሰቡ የኢኮኖሚ ዘለቦች ጋር ተጣምሮ የሚገለጽ ነው።
ይህም ማለት ከአንዱ ህብረተሰብ የኢኮኖሚ አቋሙና የምርቱን ዱ
ርጅት ሁኔታ በደንብ ለማወቅ የሚረዳው፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴያ
ች ህጎች ለማገናዘቢያ የሚውለው ፖለቲካል ኢኮኖሚ ሲሆን፣ ከዚ
ሁ አጠቃላይ ሳይንስ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች ይመነጫሉ። ፖለቲካዊ
ጥያቄዎች በዴርጅት ውስጥ በርዕዮተ ዓለም ይተረጐማሉ።

ማንኛውም ዓይነት ኅብረተሰብ አመሰራረቱ፣ በህብረተሰቡ
ም ውስጥ የሚካሄደው ማንኛውም ዓይነት ኅብረተሰባዊ ለውጥ የሚ
ራመደው በደንብ ወይም በሕግ ነው። ማርክስና ኤንግልስ ባደረ
ጉት ጥልቅ ሳይንሳዊ ትንተና መሠረት የማንኛውም ዓይነት ህብረ
ተሰብ አካሄድ፣ ዕድገትና ልማት በዚያውም መጠንም ለውጡን የሚ
መራው ደንብ ወይም ሕግ መኖሩን ገልፀዋል። ይኸውም ደንብ የ
ሚመነጨው ከህብረተሰቡ የስልተምርት አደረጃጀት ነው።

የኅብረተሰቡ የፖለቲካ፣ የሕግ፣ የርዕዮተዓለም የቤተ
ሰብና የሰያች ዕለታዊ /የሰርክ/ ኑሮ ግንኙነቶች ሁሉ የሚቋቋ
ሙት፣ አድገው የሚለመልሙት በህብረተሰቡ የምርት ግንኙነቶች ላ
ይ ያረፈ ነው። የህብረተሰብን ዓይነት፣ አቋሙን፣ የመደቦችን
የህብረተሰብ ወገኖች ቦታ፣ የሕዝብን የማቴሪያልና የመንፈሳዊ
ጥቅሞች የሚወስኑት ገንነው የሚገኙት በህብረተሰቡ ውስጥ ያለው
የምርት ግንኙነት ይሆናል። የምርት ግንኙነቶች የህብረተሰቡ
ሕንፃ መሠረት ሲሆኑ ማርክስ እንዳለው የምርት ግንኙነቶች የ
ህብረተሰብን መሠረት ጥለው የፖለቲካውን ሐይል ጠባይ፣ የመንግ
ሥትን መመሪያ፣ የህብረተሰቡን የመደቦች አቋም ይርስናሉ ብሏል።
የምርት ሁለት ዐቢይ ክፍሎች ማለትም የምርት ሃይሎችና የምርት
ግንኙነቶች የማቴሪያል ሐብት የሚደራጅበትን ሁኔታ፣ ባህልንና
ስልጣኔ የሚፈጠርበትን ጉዳና የሚያንፁ ናቸው። ሰያችም የማቴ
ሪያል ፍላጐታቸውን ለማርካት በሚያደርጉት ጥረት ርስ በርስ በ

ተወሳሰበ መረብ ይያያዛሉ። ይህ የምጣኔ ሐብት ዘለበት የህብረሰቡን አባላት የሚያስተሳስራቸው ዓይነተኛ መለያ ሆኖ ይዘልቃል።

የምርት መገልገያዎች ይዞታ በህብረተሰቡ ውስጥ የተፈጠረውን የማቴሪያል ሐብት በማከፋፈል ረገድ መሠረታዊ ሚና አለው። በዘባቻና ተበዝባቺ በሰፈነበት ሥርዓት ምርት ማምረት ህብረተሰባዊ ሆኖ የምርትን ውጤት ወይም ፍሬ በማከፋፈል ረገድ ግን ግላዊ ነው። ይህን መሳይ ህብረተሰብ ውስጥ ገኖ የሚሰራበት መርህ ወይም ፕሪንስፒል ብዙሐኑን የሚበዘብዙ ጥቂቶችን የሚያበለጽግ ነው። ይህ የምጣኔ ሐብት ብዝበዛ ወሰን የሌለው በመሆኑ ከዚህ የሚመነጨው ቅራኔ በሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያሳድራል። የድርጅቶቹ አባላት በተሰማሩበት የኑሮ መስክ የሚያጋጥማቸው ችግር ፖለቲካዊ፣ ርዕዮተ ዓለማዊ ትርጓሜን በመያዝ የጠባብ ፍጭት ይደረገባቸዋል። በዚህ ሥርዓት ውስጥ በመንግሥት ሐይል፣ በመንግሥት የድርጅት ተቋሞች፣ በሕግ፣ በአስተሳሰብ ወ.ዘ.ተ የሚንፀባረቁ በደሎች ሁሉ የአገዛዙ ባህሪ የብዙሐኑ አካል አለመሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው።

አንድ ሕብረተሰብ የደረሰበት የልማት ደረጃ /ትዕይንት/ በሕብረተሰቡ አባላት የንቃተ ህሊና ላይ ከፍተኛ ግፊት ያሳድራል። በጠቅላላው በብዙሐን ድርጅቶች ውስጥ ዋናው የውይይት መንፈሱ አቀጣጫው በድርጅቶቹ ዓላማና ተግባር ላይ ያረፈ በመሆኑ እንደድርጅቶቹ ዓላማ ተግባር መሠረት በተጨማሪም እንደታቀፉት አባላት የንቃተህሊና ደረጃ ድርጅታዊ ውይይቶችም ሆኑ የድርጅቱ አባላትን የጋር ጥቅም የሚመለከቱ ጥያቄዎች ሁሉ ሥርዓቱ የፈጠራቸውን ችግሮች በመቃወም ላይ ያረፈ ይሆናል።

ለውይይታችን እንዲያመቸን የብዙሐን ድርጅቶች ከምንላቸው የሶሻልና የሙያ ድርጅቶችን ብቻ ባይሆኑ ፖለቲካል የሆኑትን የብዙሐን ድርጅቶች እናነሳለን። ጋጠውም ኒዩ ኮሎኒያል በ



ሆኑ አገሮች ውስጥ ምንም እንኳን ከህብረተሰቡ ቁጥር ጋር ሲነፃፀር በጣም ጥቂቶች ቢሆኑም የሠራተኛው ማኅበር፣ የወጣቱ ማኅበር በቁጥር ካመዘነው ደግሞ የገበሬ ማኅበራት የብዙሐን ድርጅቶች የመቋቋሚያቸው ዋና መዳረካቸው ያረፈው የድርጅቶቹ አባላት በኑሮአቸው ላይ የሚያጋጥማቸውን ችግር ለማስወገድ የሚጠቁበት ድርጅታዊ ሃይል ሲሆን፣ በድርጅቱ ውስጥ የሚሰፍኑት የፖለቲካ ጥያቄዎች በቀጥታ ከሕብረተሰቡ ውስጥ የሚመነጩ ቅራኔዎች ነፀብራቅ ነው። ህብረተሰቡ በመደብ የተከፋፈለ እስከሆነ ድረስ መንግሥት የሚባለው ክፍልም የአንዱን መደብ ጥቅም ጠባቂ ይሆናል የዚህ ጥቅሙ የሚጠበቅለት መደብ የብዙሐን ወገን የሚበዘብዝና የሚያደኸይ እስከሆነ ድረስ የብዙሐኑ ድርጅቶች ባለጥቅሙን ወገን በአነስተኛ ደረጃም ቢሆን ለመታገል፣ ጥቅማቸውን ለማስከበር ሁኔታው በሚፈቅደው መሠረት በቀስ ቀኝ፣ በመፈክር፣ በጥገናዎች ጥያቄ በተሸፈነ የፖለቲካ ንቅናቄ የትግል አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል።

በብዙሐን ድርጅቶች ንቅናቄ ውስጥ የፖለቲካ ጥያቄዎች ከሕብረተሰቡ መሠረት ከሆነው ከማቴሪያሊዊና የሶሻል ጥቅሞች በደሎች ይመነጫሉ። ይህን አጠቃላይ የህብረተሰቡን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ መንፈሳዊ ሁኔታዎችን ማገናዘቢያ መነፅር ርዕዮተዓለም ነው። ይህ ርዕዮተዓለም ቀደም ሲል እንደተገለፀው በሳይንሳዊ አመለካከት ሊሸፈን ይችላል ወይም ከዚሁ ተቃራኒ በሆነው በአድሀሪ አመለካከት ይዋጣል። በጠቅላላው መደባዊ ባህሪ ይኖረዋል። ከመደብ ጥቅም በሚመነጩ የማቴሪያልና የሶሻል የመንፈሳዊ ፍላጎቶች ጋር የተጣመረው አመለካከት ርዕዮተዓለም ትርጓሜ ይይዛል።

የሰዎች የመደብ ጥቅም በህብረተሰቡ ውስጥ ካለው የምርት ሃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ጋር በአጭሩም ከስልተምርቱ ጋር ያላቸው ዝምድና ነው። ይህም ማለት የምርት ማምረቻ ባለቤ

ት የሆነው የአሰሪው ክፍል የመደብ ጥቅምና ጉልበቱን ለአሰሪው በመሸጥ የዕለት ኑሮውን የሚገፋው ጭቁኑ መካከል ተመሳሳይ የመደብ ጥቅም የላቸውም። ከነዚሁ ከሁለቱ ሊመነጭ የሚችለው ተፃራሪና የማይታረቁ ቅራኔዎች ይሆናሉ። እነዚህም ቅራኔዎች ሊታረቁ ከማይችሉ ባላጋራ ከሚሆኑ መደቦች የህብረተሰብ ወገኖችና ሃይሎች ፍላጎት ይመነጫሉ። እንደነዚህም ያሉትም ቅራኔዎች ትክክለኛ መፍትሄያቸውን የሚያገኙት ወይም በትክክል የሚፈቱት በመደብ ትግልና በህብረተሰቦች አብዮት ነው። የማይፃረሩ ቅራኔዎች ግን የጋራ ጥቅም ባላቸው በመደቦችና በህብረተሰብ ወገኖች መሃከል የሚገኙትና የሚኖሩት ናቸው።

ስለሆነም በአንድ የብዙሐን ድርጅት የሚደራጁት ግለሰቦች ሊታረቁ የማይችሉ የመደብ ቅራኔ ያላቸው አይደሉም። መጠነኛ የሆኑ የፖለቲካ ጥያቄን መፍቻ አመለካከታቸው ይለይ እንጂ በድርጅት ታቅፎ የጋራ ችግርን ለማስወገድ የሚኖራቸው እምነት የድርጅቱ መሠረት በመሆኑ ድርጅቱ የተቋቋመበትን ዓላማና ተግባር በሚመለከት የሚቀየሰው የትግል ጎዳና ይህንኑ የአባላቱን በሕብረተሰቡ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የሶሻል ችግሮች ያስከተለውን ቀውስ በሚመለከት የተነደፈ ነው። በትግሉ ደረጃ ለሚነሱት ጥያቄዎች ሁሉ መልስ የሚያገኙት የሰፊው አባል በውይይት መሳተፍና በድርጅቱ ዲስፒሊን ላይ አስተዋጽኦ በማድረግ ሲሆን፣ እያንዳንዱ አባል ድርጅቱ እንዴት እሱን ሊጠቀመው እንደሚችል በሚኖረው አመለካከት ሐሳቡን የመሰንዘርና ባለው የፖለቲካ ዕምነቱ ቅስቀሳ ሊያደርግ ይችላል።

የፖለቲካ ጥያቄዎችም የሚንሸራሸሩት በድርጅቱ ሰፊ የዲሞክራሲ መድረኩ፣ በታነፀበት ዲስፒሊኑ መሠረት ላይ ነው። ድርጅቱ በአባላቱ ፍላጎት ላይ የቆመ ስለሆነ አባላቱ በሕብረተሰቡ ውስጥ ባላቸው ቦታ በድርጅቱ ትግል ሂደት የፖለቲካ ጥያቄ ውስጥ ከፍተኛ ተጽእኖ አለው። ለሚነሱትም ጥያቄዎች የመፍቻው



ዋና ቅስፍ ዲሞክራሲ ውይይት ይሁን እንጂ ለጥያቄው መፍቻ የሚውሉ ዘዴዎችን በርዕዮተዓለም፣ በሌላም አንፃር ሁሉ አቀፍ የሆነ መልስ የማግኘቱ ሁኔታ ድርጅቱ የአንዱን መደብ ርዕዮተዓለም መመሪያው በማድረግ አይደለም። ከላይ እንደገለጽነው ፖለቲካው በብቦት በችግር የሚንፀባረቅ ጥያቄ ሲሆን ርዕዮተዓለሙን ድርጅታዊ ቅርጽ በሕዝባዊ ድርጅቶች ይዞ ዝንተ አለም አይኖርም። በሕብረተሰቡ ውስጥ ተፃራሪ ቅራኔዎች እየለመለሙ እየለሙ በመሀከላቸውም የሚኖረው ትግል የተባ ግጭት እየሆነ ሲቀጥል ቅራኔያቸ የበለጠ በመክረር፣ የግጭቱ መፍትሄ የሚያገኝባቸው ቅርጾች የሚወስኑት በትግሉ ታሪካዊ ሁኔታዎች ነው። ስለዚህ ፅኑ በሆነ በከረረ የመደብ ትግል የተዋጠ ህብረተሰብ ካለ በዚያች ወቅት የብዙሐን ድርጅቶች ባለው ሁኔታ በመዋጥ በመደብ ትግል ቅራኔው ውስጥ የመግባት ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

በህብረተሰብ ሂደት ውስጥ ያሉ ጥያቄዎች ሁሉ ርዕዮተዓለማዊ ትርጓሜ አላቸው። በአንዱ የመንግሥት አገዛዛዊ ባህሪ ውስጥ ያለውን የሶሻል፣ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች በማስተንተን ሁኔታው የሚሻርበትንና በሌላ ተራማጅ ሥርዓት የሚተካበትን ጎዳና የመሻቱ ፍላጎት ሁሉ ከመደብ ጥቅም ጋር የተያያዘ ርዕዮተዓለማዊ መመሪያ አለው። በብዙሐን ድርጅቶች ውስጥ ዋንኛው መለያቸውም ርዕዮተዓለማዊ የድርጅት ቅርጽ ይዘው አለመፈጠራቸው ነው። በሕዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሶሻላዊ ወይም መንፈሳዊ ጥያቄዎች ድርጅታዊ ቅርጽ ሊይዙ ይችላሉ። ለምሳሌ የሠራተኛ ማኅበራት ድርጅታዊ ቅርጽ የሠራተኛውን መደብ ጥቅሞች ለማስከበር በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚ፣ በሶሻል ያሉትን ችግሮች ለማስወገድ የሚፈጥረው ድርጅት መታገያ መሣሪያው ሲሆን፣ በርዕዮ ተ ዓለም አንድ መልክ አይዝም። ይህም ማለት የድርጅቱ የተወሰነው ክፍል በጥገና ለውጥ ሊያምኑ ይችላሉ፣ ቀሪው ወገን ደግሞ የሠራተኛውን ሚና በማቀረብ በመሠረታዊ ለውጥ ሊሆን ይችላል። ግን እነዚህ አመለካከቶች ድርጅቱ የታነፀበትን መርሀ አይሸረሽሩትም።

## የተማሪው ክፍል ከቀረው የህብረተሰብ ክፍል በምን ይለያል በምንስ ይመሳሰላል?

አንድ ሰው ተማሪ ሆኖ ዕድሜ ልኩን ስለማይኖር ተማሪነቱ ጊዜያዊ ነውና ተማሪዎች ከህብረተሰቡ የተለዩና የራሳቸው የሆነ መደብ የላቸውም:: ይህም ማለት የተማሪው ክፍል ሰዎች በህብረተሰቡ የምርት መገልገያዎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት መጠን፣ በሥራ ሕብረተሰባዊ ድርጅት ውስጥ በሚኖራቸው ሚና፣ ከህብረተሰቡም የማቴሪያል ሐብት በሚቀበሉበት ድርሻና ድርሻውንም በሚቀበሉበት መንገድ በሚለያዩ ትላልቅ የህዝብ ወገኖች ክልል ሊመደቡ አይችሉም:: በእርግጥ የተማሪው ክፍል ከትምህርት በኋላ በሥራ ሙያው በሚሰማራበት ወቅት ከቀረው የህብረተሰብ ክፍሎች ከሆኑት ጋር ይደመራል:: ይህም የኑሮ ዘይቤው ይወስነዋል::

ሆኖም የተማሪው ክፍል ከንዑስ ከበርቴው መደብ ውስጥ የሚደመር ነው:: ይህ የተማሪው ክፍል ምሁሩንም ጨምሮ አእምሮአቸው በትምህርት የታነፀ ከትምህርት ከምርምር ያልራቁ ናቸው:: ዕውቀት በሚያስገኝላቸው ትምህርት አማካይነት ንቃተ ሀሳብ ያገኛሉ:: ንቃተ ሀሳብ ሰው ነገራዊውን አለምና የራሱንም መሆን ወይም ሀሳቡ የሚያገናዝብበት የልቡና ሂደቶች ጠቅላላ ድምር ነው:: በመሠረቱ ንቃተ ሀሳብ የህብረተሰቡ የልማት ውጤት ነው፡ በስራ ሂደትና በህብረተሰብ ግንኙነቶች ማለትም አንዱ ከሌላው ጋር ከሚያደርገው የህብረተሰብ ግንኙነቶች አማካይነት ሰዎች ከአካባቢው ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት ለማገናዘብ በኑሮአቸውም ላይ ዓላማ ያለው ስራ የሚፈጽሙበት የህብረተሰብ ልማት ውጤት በሆነው በንቃተ ሀሳብ አማካይነት ነው::

ይህ ንቃተ ሀሳብ በድርጊት ቅርጽ ይይዛል:: ይህ በፊንታው ደግሞ ይህን ድርጊት እየወሰነና እየተቆጣጠረ በተጽእኖ ይመራዋል:: የተማሪው ክፍል ንቃተ ሀሳቡን የሚያገኘው የበዝበዛ ሥርዓቱ የሚያስከትለውን የተዛባ የህብረተሰብ ሁኔታ መገንዘብ ሲጀምር ነው:: ስለሆነም የተማሪው ክፍል በህብረተሰቡ ው-



ስጥ ያሉትን አጠቃላይ የፖለቲካ፣ የሶሻል ግንኙነቶችን ከግል ጥቅሙ ጋር በማነፃፀር የወደፊቱን ዕድሉን ጥርጊያ መንገዱ መከፈቻ በሚውል የትግል መስክ በመሰማራት በትምህርት ዕድል ያካበተው ዕውቀቱ ድርጊትን እንዲፈጥር ይረዳዋል:: ይህ ዕውቀቱ ድርጊታዊ ቅርጽን በመያዝ በህብረተሰቡ ውስጥ ተስማሚ መፈክሮችን በመምረጥ ይታገላቸዋል::

በኛ ዓይነቱ ህብረተሰብ ውስጥ የተማሪው ክፍል እንደቀረው የህብረተሰቡ ጭቁን ክፍል የሚጋራው በደል ብዙ ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ የተማሪው ክፍል የሚፈጥረውን ድርጊቱን በዲሞክራሲ መንፈስ የተማሪውን ጥቅም ለማስጠበቅ ለመታገል ይሻል:: እነዚህም ጥቅሞች ከህብረተሰቡ አባላት አጠቃላይ አቃጣይ ጥያቄዎች ጋር ከተያያዙ የትግሉ ትኩረት ብዙ አቅጣጫዎችን ይይዛል:: የድርጅት ነፃነት፣ የመወያየት፣ የሕብረተሰብን ዕድገት ሕግጋት ለመማር ለማስተማር፣ ተማሪ ከትምህርት በኋላ በቂ የሥራ ዕድል እንዲያገኝ፣ የትምህርት ሥርዓትና ይዘት በአገሪቷ ትክክለኛ የዕድገት አቅጣጫ እንዲቀየስ የመሳሰሉት የተማሪው ክፍል የመታገያ ጥያቄዎች ናቸው:: እነዚህ ሁኔታዎች ለብቻቸው ተነጥለው በተማሪው ክፍል ላይ ብቻ አይገደቡም:: የድርጅት ነፃነት በአገሪቷ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝን ይጠይቃል:: ነፃ አስተያየቶች በድርጅቶች እንዲንሸራሸሩ፣ ድርጅቶች በአባሎቻቸው ንቃት እንዲመሩ እንዲጎለምሱ በአገሪቷ ውስጥ የተስተካከለን አስተዳደርን ይጠይቃል:: ተማሪው ለወደፊቱ በተማረው መሠረት በቂ የሥራ ዕድል እንዲያገኝ ጥንቃቄ መደረጉ ለአገር ብልጽግናና ሥልጣኔ ለህዝቦች ደህንነት የሚበጅ ፖሊሲ የሚከተል መንግሥት ያስፈልጋል::

የተማሪው ክፍል እነዚህንና ሌሎችንም ጥያቄዎች ሲያስላስል ሁኔታውን በትክክል ለመረዳት አግባብ ካላቸው ነገሮች ጋር በማዛመድ የህብረተሰቡን ቅራኔዎች መመልከት በሚጀምርበት ወቅት

በራሱ በተማሪው ክፍል ላይ የሚንፀባረቁት ችግሮች መሠረታቸው ህብረተሰቡን ከሚገፉት ቀራኔዎች ጋር የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ለመገንዘብ ዕድል ይኖረዋል:: የተማሪው ክፍል የህብረተሰቡንም ጥያቄዎች ቢሆን ከራሱ ጥቅም ዉጪ አያያቸውም:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ መታየት የሚገባው በትግል አንፃር ሲታይ የተማሪው ክፍል የራሱ የሆነ መደባዊ ፀባይ ያለው ባለመሆኑ ትግሉ ግብታዊነት ያጠቃዋል:: ይህም ማለት ርዕዮተአለማዊ አመለካከት በጥራት የበላይነት ሊይዝ ስለማይችል ነው::

ከላይ እንደተጠቀሰው የተማሪው ክፍል በትምህርት ገበታ አካባቢ በመሆኑ በሕብረተሰብ ጥያቄ ላይ የተፃፉ ፅሑፎችን ወይም ሌሎችን የተፈጥሮ ሳይንሶችን ከሌሎች የተበደሉ ክፍሎች የበለጠ ቀደም ብሎ የማንበብ ዕድል ይኖረዋል:: ወጣቱም የተማሪ ክፍል አዲስ ሐሳብን የመቀበል መለያ ፀባይ ስላለው በተራማጅ ተግባሮችም ውስጥ የመሳተፍ ዝንባሌ ያሳያል:: በሌላው በኩል የተማሪው ክፍል በአንዱ መደብ ላይ የቆመ ባለመሆኑ ነገራትን ሁሉ በሳይንሳዊ መንገድ የመፍታት ኃይል የለውም፤ትግሉም ግብታዊ የቈሳበት የሚሆነው ለዚሁ ነው:: ይሁን እንጂ በትምህርት ቤት አካባቢ ባለ ያገኛቸውን አዲስና ተራማጅ ትምህርቶች ለራሱ መጠቀሚያና መሳሪያ ሳያደርግ ሌሎችም የተበደሉ ክፍሎችን በመስለው ዘዴ ለማስተማር ጥረት ያደርጋል:: ከዚህ አንፃር ሲታይ የተማሪው ክፍል የማይናቅ ክፍል ነው:: ምንም እንኳ የወጣቱ ክፍል እንደሌሎቹ በሥርዓቱ ቢበደልም ቀሉ በትምህርት አካባቢ በመገኘቱ ብቻ ከሌሎቹ የበለጠ ነገራትን በሁለት በኩል ያዩ መንገዶች ማለት በላብአደሩና በከበርቴው መነፀር ሲተረጉማቸውና የዚህ ወይም የዛኛው አባሪ ሊሆን የሚያስችል አዝማሚያ ስላለው በጣም የሚለይበት ነጥብ ነው:: ስለዚህ ላብአደሩ የተማሪውን ክፍል እንደሌሎቹ የሕብረተሰብ ወገኖች በፖለቲካ በርዕዮተዓለም በድርጅታዊና በቀሩትም ትክክለኛውን መንገድ በማስያዝ በማንኛውም ረገድ ለአብዮቱ አባሪ ማድረግ ግዴታው ነው::



## <u>የተማሪው ድርጅታችን የትግል መርሆ ምን መሆን አለበት?</u>

የተማሪው ድርጅት ተግባሩን በሚቀይስበት ወቅት ተጨባጭ ሁኔታዎችን በቀጡ ማጤን ይኖርበታል:: በአሁኑ ወቅት በአገራችን ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝና የህዝቦች እንቅስቃሴ ምን ሁኔታ ላይ እንደደረሰ ካለመታከት ማውጠንጠን የወቅቱ ግዴታ ሆኖ መታየት ይኖርበታል:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች የዉጪ ሃይል አለፍላጎታቸው እንዲያስተናግዱ ቢበየን የህዝቦችን ሰፊ ድጋፍ አገኝቶ አይደለም፤ የቤተመንግሥት ጓሉታ እንጂ! የኢትዮጵያ "ነፃነት" ሰላም ወዳጅ በሆኑ በዓለም ውስጥ በሚገኙ ሕዝቦች ትልቅ የጥያቄ ምልክት ለምን ተደረገበት? የአገራችን ህልውና በኢኮኖሚ፤ በሚሊተሪ፤ በፖለቲካ በሌሎችም ለምን ተገፈፈ? አገራችን ነፃ የምጣኔ ሐብት ዕድገት ጎዳና ለመምረጥ ትችላለች? አቀጣጫውንስ ይዛለች? የኢትዮጵያ ሕዝብ የሥራው ውጤት ባለቤት ነው? የልዩ ልዩ ብሔሮች ንቅናቄ ለምን እዚህ ደረጃ ደረሰ? የወጣቱ ክፍል በአገሪቷ የዕድገት ጎዳና ተሳትፎው እንዴት ነው? አገራችን ዛሬ ያለችበትን ምስቅልቅል ሁኔታዎች እንዲህ በዝርዝር ማቀረቡ ቀላል አይደለም::

የተማሪው ድርጅታችን የፖለቲካ ድርጅት ነው:: የፖለቲካ ድርጅትነቱ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሰፊ የዲሞክራቲክ ንቅናቄ ሲያደርጉ በነበረበት ወቅት እንስቶ የህዝቦችን ንቅናቄ ከራሱ የግል ጥቅም ጥያቄዎች ጋር በማቀናጀት በመታገል በአቋም ደረጃ፤ በመድረክ ደረጃ ሚና የለየ ድርጅት በመሆኑ ነው:: በአሁኑ ወቅትም በአገራችን የተፈጠሩትን ሁኔታዎች ከብዙሐን ድርጅታችን አጠቃላይ ፀባይ ጋር በማጣመር የአባላቱን የግል ፍላጎትና ዕምነት ትክክለኛ ድርጅታዊ ቀርጽ ይዞ እንዲቀጥል ለማድረግ ብቁ መሆን ይኖርብናል::

በዉጪ ያለው ወጣት ቁጥር ስፍር የለውም:: ያለበትም አኗኗር ሁኔታ ብዙ የስቃይ ማህደሮች የሚፈራረቁበት ቢሆን

ከዐለታዊ ኑሮ ማሸነፍ ትግል አንስቶ በትምህርት ቤቶች አካባቢዎች በመዋል ብዙ ውጣ ውረዶች ያሉበት የኑሮ መስኮች ይገኙበታል:: በዉጪ ካለው ወጣት አብዛኛው የኑሮ ስቃይን የሚያስተናግዱ ሲሆን፣ በጣም ጥቂቶች ደግሞ የዚህ አደጋ የሌለባቸው አሉ፡ ገን አንዱ ተመሳሳይ፣ የጋራ የሆነ ጥያቄ አለን:: መገባባትም ያለው በአገራችን ያለው ሁኔታ ለበደት ያበቃን መሆኑን ለማገናቸንም ገለጸ ነው:: ሰፊ ዲሞክራሲ የመደረጃጃ ዓይነተኛ መሣሪያው የሆነው ድርጅት፣ በድርጅቱ መታቀፍ የሚገባቸውን ኃይሎች ጋር አብሮ ለመታገል ሁኔታውን መፍጠር ይኖርበታል:: በአሁኑ ወቀት ግዙፍ የሆኑ በአገራችን ገነው ሚገኙ ጥያቄዎች የመስማሚያ ነጥቦች ሆነው መገኘት ይኖርባቸዋል::

ከላይ እንደተገለጸው ወጣቱ በጠቀላላው በባዐዱ አገር ፈቦ ይገኛል:: በዉጪ አገር ያለውን ዐንገዱኛነት በመጠኑም ቢሆን ለመዉጣት፣ የሚበሉትና መጠጊያ ያጡትን ወንደሞቻችንን በአፍሪካ ምድር የሚገኙትን ኢትዮጵያዊ ስደተኞች ለመርዳት፣ ጠቀኛ የመዉያያ፣ ትምህርት የመገበያያ፣ ወጣቱ የገዛ አገሩን ሁኔታ በመከታተል አስተያየት የሚያቀርበበት፣ የማኅበራዊ ኑሮዎችን የሚያቀናጁበት፣ የህብረተሰብ ለውጥ ህገጋትን የሚወያይበት ሰፊ ዲሞክራቲካዊ ንቅናቄ መፍጠር አስፈላጊ ነው::

በርገጥ የተማሪው ድርጅት አባላት ዋና መሠረቱ ተማሪው ምሁሩ ነው:: በአሁኑ ጊዜ የድርጅቱም መሠረት መጣል ያለበት በዚሁ ክፍል ብቻ አድርጌ መቀጠሩ የወቀቱን የአገራችንን ሁኔታ በሚገባ አለመረዳት ይሆናል:: በህዝቦች ትግል ዉስጥ በልዩ ልዩ ጊዜያት የተገሉ ደረጃና አቀጣጫ ለመገንዘብ ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው:: ድርጅቱ ቢበረታ ጫወሰ ከድርጅቱ አባላት የመደብ ባህርይ ከመደብ ፍላጐታቸው ጥቀማቸው ስለማያልፍ የድርጅቱ የመታገያ መድረክ የተወሰነ ገደብ ይኖረዋል:: ድርጅቱ የፖለቲካ orientation ያለው መስክ ይዞ መራመዱ ይኖርበ



ታል:: መደራጀትና መደረጃጀት የወቀቱ ግዴታችን ነው:: የድርጅቱ መኖር ተፈላጊነቱ ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ሁኔታ መማርን፣ እንደ ህዝቦች ሁኖ መኖርን፣ የህዝቦችን አርሮዎች ሁሉ ሲያንፀባርቀ የሚችል መሆን ይገባዋል::

ድርጅቱ ሁኔታዎችን ለመቀጠርና በራውንም ለመምራት በአገራችን ሁኔታዎች ላይ ቀስጥ ያለ አቋም እንዲኖረው ያሻል:: በሰ ዲሞክራሲ ቢወባ፣ ዲሞክራሲ የድርጅቱ መቋቋሚያ፣ መጠናከሪያ የሆነ መመሪያው ነው ሲባል፣ የተወሰኑ ዲስፒሊኖችንም አይኖሩትም ማለት አይደለም:: እንዳውም እዚህ ጋር አብሮ መታሰብ ያለበት ድርጅቱ ባለው የፖለቲካ አቋሞች አንፃር በዲሞክራሲ ዋህዱነት ለመተዳደር መቻል ይኖርበታል:: ይህን መርህ ድርጅቱ በቻሉታው አንፃር መገለገል ይኖርበታል::ይህም በአጭሩ የሰፊ ዲሞክራቲክ ውይይት ውጤት ማዕከላዊ አመራር መያዝ፣ ማኅበራዊ አመራር፣ ሕጋዊ መመሪያዎች፣ ሂሶች መጠቀም ማለት ነው:: ዲሞክራሲ ያለ ዋህዱነት ገደብ የሌለው ነፃነት ማለት ነው:: የድርጅትን መዝረክረክ ያስከትላል፣ ውሣኔዎችን በሥራ ላይ ማዋል ያግዳል፣ አንዱነት ወይም ዋህዱነት ያለ ዲሞክራሲ ደግሞ በፈንታው አምባገነንነትን ያስከትላል:: ሁለቱንም አጣምሮ መያዙ ድርጅቱ ፖለቲካዊ ድርጅት ለመሆኑ አንዱ መለኪያው ነው::

አንዱ ነገር ከህብረተሰቡ ንቅናቄ ከድርጅቱ አባላት ህይዎታዊ፣ አስምሮታዊ ተግባር ስሜታዊ ዝንባሌና ፈቃዱ ዉጪ ሊታይ አይችልም:: ይህም በመሆኑ ድርጅቱ ለህብረተሰባችን ነፃ ዕድገት፣ ለሕብረተሰባችን ዲሞክራሲ መስፈን፣ ለርትአና ለፍትህ ለአገር ነፃነት ህልውና የመቀር ቀር ጥያቄ ላይ ሚና መያዝ የድርጅቱ ዋንኛ መለኩ መሆን ይገባዋል:: ይህም ማለት የህብረተሰባችን ዕድገት የሚቀጥ የሚያጨጨ ጉዳናዎች መስፈናቸው፣ የበጨርቸና የበጨረሰቦችን ዲሞክራቲካዊ ጥያቄዎች አለመፈታታቸው፣ የአገሪቱ ጥሬ ጠብቶች ያለአንዳች ገደብ የበዝበዛ መርሆ ባነገቡ

አገሮች መዘረፋ፣ ሕዝቡ በሰላም ለመኖር አለመቻሉ፣ በረሃብ አለንጋ መገረፉ በጠቀለለው የሀብረተሰባችንን ኋላ ቀርነት ዋና ዋና ምክንያቶችን በመተንተን በአቋም ደረጃ የድርጅቱ መድረክ የሚተለሙበት አካባቢያች ዋነኛ ነጥቦች መሆን ይገባቸዋል:: ይህም ቢባል በጠራዊ ስሜት ያጣው ዋነኛ የገጠመው ሃይል መለያ ጠባዩን፣ ኢዲሞክራሲያዊ ፖሊሲው አምባገነናዊ አገዛዝ ወጣቱ በትኩረት ማየትና መታገል የሚገባው ጥያቄ ነው::

ድርጅቱ የሕዝብ ወገን፣ ለዲሞክራሲ የቆመ ሃይል፣ ተቃዋሚ ሃይል የሚሆነው በአገራችን ያለውን ሁኔታ ከአባላቱ የግል ጥቅሞችና ፍላጐቶች ጋር አያይዞ የመታገል ችሎታ ቢኖረው ነው: ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት የመታገያ መድረኩ ተከከለኛ መርሆዎች የሚነደፉበት ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአንዱ በኩል፣ አምባገነናዊ የወታደሩ መንግሥትና የሶቪየት ሕብረት በሌላ በኩል በመሆን ዲሞክራሲ ንቅናቄዎችን ሁሉ ለመደምሰስ ታጥቀው ከተነሱ ሰንብቷል:: የሶቪየት ሕብረት በአገራችን ያለውን ሁኔታ በማባባስ ስራ ሚና እየተጫወተች ነው:: የትግላችንም ትኩረት የሕዝቦች አንድነት፣ የሕዝቦች የተባበረ ክንዱ ወደ ዋና ጠላት ላይ ማረባረብ ይሆናል::

በፊውዳል ሥርዓት ማኅደር ውስጥ ያሉት ዐይነተኛ መደቦች የመሬት ከበርቴዎችና የገባር ወይም የጪሰኛ ገበሬዎች መደብ ወይም በመሬት ከበርቴውና በገባሩ መካከል የሚኖረው የምርት ማለትም የኢኮኖሚ ግንኙነቶች በአገራችን ውስጥ በአዋጅ ተሸረዋል::ጥያቄው ያለው እንግዲህ በፊውዳል ሥርዓት ማህበር ውስጥ ሊታዩ የሚችሉት ለሥጋዊ ኑሮ የሚያስፈልገውን የማቴሪያል ሃብት የሚወስነው የመሬቱ ይዘት፣ ሀብቱ የሚገኝበት ሁኔታ፣ ሀብቱን የሚፈጥሩት መሣሪያዎች ገና በአገሪቱ ውስጥ መሠረታቸው ተነክቷል ወይስ አልተነካም? ይህስ በፊንታው የስልተምርቱን ዕድገት ያራምደዋል ወይስ ዕድገትን ይቀጪል? ጠቁ ያለው ከኋለኛው ምርጫ ላይ ነው:: በተጨማሪም በፊውዳል ሥርዓት ቀሪቱ ዋነኛው የ



ባህል መርሀ የአንዱ ብሔር የአንዱ ወገን ባህል ከፍ ብሎ የሌላው ዝቅተኛነት የሁሉም በእኩልነት ታይቶ እንዳይሰራበት፣ የአንዱ ወገን ቋንቋ ተከብሮ የሌላው የሚናቅበት፣ መከባበር የመፈቃቀር፣ በሃይል ባይሆን በፈቃዱ የተለያዩት ህዝቦች ባንድነት የሚኖሩበት አዲስ ባህል ለማለምለም የማይፈቅዱበት ፖሊሲ እንዳለ አገዛዙ ጨብጦታል:: ይህም ከምርቱ ጋር ተጣምሮ የተያያዘ በመለኪያም የዕድገት ጉዳና ከለዩ ለዩ ባህሎች መለኪያም መለኪያው ተመርጦ በማፍኛት የብዙሐን ባሕል ዘር ለመዘራት አልቻለም:: በእርግጥ አለዲሞክራሲ የብሔረሰቦችን እኩልነት አመጣለሁ የሚለው የገጠሙ ጥገናዎች ሁሉ ከንቱ ጥረት ሆነዋል:: የነዚህና የሌሎችም ችግሮች መንስኤ የሆነው የብሔሮችን ንቅናቄ አጧጡፎታል:: ይህ የሚያሳየን ፀረ ፊውዳል ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል መደረግ እንዳለበት ነው::

እስከ 1974 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕዝቦች የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አምረው ቢታገሉ ኖረዋል:: ለዚህም ከፍተኛ የሆነ ደም ከፍለውበታል:: ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል በማድረግ ደረጃ የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ብዙ የሚያኮሩ ታሪኮችን ሕያው አድርገው ለታሪክ ማህደር አበርክተዋቸዋል:: ደግሞ አገሮችን አንድ ቀርጪ ለመከፋፈል የተደረገውን ዱለታና ወረራ በማክሸፍ የኢትዮጵያ ህዝቦች ለተተኪው ትውልድ የማይዘነጋ ወኔ፣ ጀግንነት በጠራዊ ስሜት የተመላበትን አውርሰውናል:: የአገራችንንም ነፃነት አቆይተውልን ነበር:: ምንም እንኳን ከዚያ በኋላ የወራሪዎች ዘዴ መሰኩ ተለዋውጦ ሃይለ ስላሴ ለአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም አገሪቷን አሳልፎ ቢሰጣትም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለትግላቸው እፎይታ አልነበራቸውም::

የ1974 ዓ.ም የትግል ማዕበል ዋና ትኩረቱ ነፃና ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያን ለመገንባት፣ የብሔረሰቦችን እኩልነት ለማስጠበቅ የውስጡንና የውጪውን ጠላቶች ለማንበርከክ የኢትዮጵያ

ህዝቦች እጅ ለእጅ ተያይዘው ታግለዋል። ዛሬ ያ ሁሉ መስዋዕትነት፣ መራራ ትግል በአዲሶቹ ገዥዎች ተክደ አገሪቷን የባርነት ሰንሰለት ውስጥ አስገብተዋታል። ዛሬ ባልተመጣጠነ የኢኮኖሚ ክልል ውስጥ ለመያዝ፣ የጦር ሰፈሮችን ለማደራጃ ባላት ጥድፊያ ሶቭየት ህብረት በአገራችን ላይ አድራጊ ፈጣሪ ሆናለች። የወታደሩ መንግሥት ከጥቂት ዓመቶች በፊት የ20 ዓመቶችን የባርነት ውል እጅ ከወርች ያስያዛት የኢትዮጵያ ነፃነት እስከምን ደረጃ እንደተደፈረ በቂ ህያው የሆነ ምሥክር ነው። የአገራችን ብልጽግና ጉዳና የራሱን ጥቅም በሚያባዱ፣ በርካሽ ጥሬ ሐብቶችን በሚዘርፍ ሃይል ተደናቅፏል። ይህን ሁኔታ ለመከላከል የማይችል ለሶቭየት ህብረት በይፋ ያደረ ፀረ ዲሞክራቲክ መንግሥት በመሆኑ ከጊዜ ወደጊዜ ከድጡ ወደ ማጡ እየገባ ነው። ይህም ማለት ከሶቭየት ህብረት ጋር ጥምራ በመሆን ለሕዝቦች ደህንነት ደንታ የማይሰጠው መሆኑን በይፋ እያሳየ ነው።

የሶቭየት ህብረት አሁን ባለንበት ዘመን በአዲስ መልክ ሰብአዊ ይሉኝታ በማይገኝታው ፖሊሲ፣ በአብሪተኝነት ፖሊሲ፣ የተጽእኖ ክልሎችን በቁጥጥሯ ስር ለማድረግ በአገራችን ላይ የሚፈጽመው ግፍ አገር ወዳድ ለሆነ ሁሉ፣ ለሠራተኛው ለገበሬው ለወጣቱ ለምሁሩ ለዲሞክራቱ ሁሉ ለአንዳፍታም የሚዘነጋ አይደለም።

ስለ ሃያል መንግሥታት በተለይም ስለኢምፔሪያሊዝም ከታሪክ ማኅደሮች ምን እንማራለን?

የቀድሞ ወራሪ ሃይሎች መለከታቸው አንድ ነበር። ሃያል የሚባሉት ደካማ አገሮችን ለመዋጥ የሚያሰፈስፉትና የገፈፋ ዕቅዳቸውን የሚያሟሉት በጦር በደረጀ የወታደር ሃይል በገዱ በመውረር፣ የራሳቸውን ዜጋ በመሾም፣ ቀጥተኛ የቅኝ ግዛት አስተዳደር ውስጥ በማስገባት ነበር። የምዕራብ አውሮፓ የሞኖፖል አንድነት ማህበሮች የቅኝ ግዛት ተስፋፊ ፖሊሲያቸው ለከበርቴው ሐብት ማግበስበሻ የሚውሉ ርካሽ የሠራተኛ ሐይልን ፍለጋ፣ ጥሬ



ሐብቶችን ለመዝረፊያ፣ ለሸቀጦች ገበያ ሽሚያ ላይ ያተኮረ ነበር። በምዕራብ አውሮፓ የሞኖፖሎች ገና መሰልጠን በታሪክ የታየው የተለያዩ ገጾችን በዐብሪተኝነት በተወጠረ ፖሊሲ ዓለምን በተጽእኖ ክልሎች ከፋፍሎ በምጣኔ ሐብት ወደኋላ የቀሩትን ሐገሮች በመጀመሪያ የፖለቲካ ተገዥ፣ በመጨረሻም በራሳቸው ቁጥጥር ስር በማዋል ቅኝ ግዛት ጥገኛ ሐገሮች በማድረግ በምዝበራ ዘዴያቸው መመዝበር ቢጀምሩ ነው።

የከበርቴው የነፃ ውድድር መርሆ በጥቂት ከበርቴዎች ሐብት መካበትና መደለብ እየተተካ በይበልጥ በካፒታሊስቶቹ በሞኖፖል መዋጡ ብቅ ካለበት ጊዜ አንስቶ በዓለም ውስጥ የሚገኙ ደካማ አገሮች በልዩ ልዩ መንገድ ነፃነታቸው እየተደፈረ አሁን አለንበት ወቅት ድረስ አዘግሟል። በሃያኛው ምዕተዓመት በሚጀምርበት አካባቢ ዓለምን በሙሉ ዐበይት የሚሆኑት የካፒታሊስት አገሮች ተከፋፍለውት ነበር። እስያ፣ አፍሪካ፣ የቅኝ ግዛት ልዩ ክልል በመሆን ተለውጠው ነበር። የምድርን ገጽ 2/3ኛውን የሚሸፍኑ አገሮች ከዓለምም ህዝብ ሁለት ሶስተኛው የሚሆነው በቅኝ ገዥዎች ቀንበር ስር ወድቆ ይማቀቅ ነበር። በቅኝ ግዛት ምዝበራ ከሁሉም ንቁ የነበሩት እንግሊዝ፣ ፈረንሣይ፣ ፖርቱጋል እስፓኝ ሌሎችም ነበሩ።

አሁን ባለንበት ዘመን በሃያኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛው አጋማሽ ጀምሮ የኢምፔሪያሊስት ሐይሎች ወደኋላ የቀሩትን በቅርቡ ለይስሙላ ነፃነታቸውን ያገኙትን ሀገሮች የምጣኔ ሐብት ጥገኛቻቸው ለማድረግ የተቻላቸውን ሁሉ በመፈጸም ላይ ናቸው። የእነዚህን አገሮች ልዩ ልዩ የምጣኔ ሐብት ቅርንጫፎች በቁጥጥራቸው ስር ለማደረግ፣ በምጣኔ ሐብቱ ውስጥ ቁልፍ ቀልፍ የሆነውን ሥፍራ በመያዝ ዐቢይ የሆኑትን የኢምፔሪያሊስቶች የሞኖፖሎች ማህበር እነዚሁን ሐገሮች ወደገለ ቢተርስትነት ለመለወጥ ጥረዋል። ይህ ብቻ አይደለም ታላላቁ የኢምፔሪያሊስት አገሮች የእነዚህን አገሮች የፖለቲካ ሀይፃቸም በጥብቅ ይቆጣጠ

ራሱ:: ፕሬዘዳንቶቻችንና ጠቅላይ ሚኒስተሮቻችን ከሥልጣናቸው እን
ዲወርዱ፣ መፈንቅለ መንግሥቶች እንዲደረጉ፣ ተቃዋሚ ገለበጣዎ
ች እንዲካሄዱ ያደርጋሉ::

በኢምፔሪያሊዝም ዘመን ካፒታሊዝም ያደገው በተለይ ባል
ተስተካከለና ግጭት በበዛበት አኳኋን መሆኑን ሌኒን አመልክቷ
ል:: ይህንንም አለመስተካከል የሞኖፖሊዎች የተፋጠነ ዕድገትና
የቴክኖሎጂ የተቻኮለ ርምጃ አባብሶታል:: ቀደም ሲል ከሁሉ ጠ
ንካራ የነበሩትና ግንባር ቀደም ሆነው የተነሱት ሀገሮች በኋላ
በሌሎች ወደጐን ተገፉ:: ለምሳሌ እንግሊዝ ለረጅም ጊዜ በምጣ
ኔ ሐብት ከሌሎች አገሮች ቀድማ ተገኘ ነበር:: በሃያኛው ምዕ
ተ ዓመት መጀመሪያ ላይ የዓለምን የምጣኔ ሐብት መሪነት አሜሪ
ካ ስትይዝ ጀርመን ደግሞ የአውሮፖን የምጣኔ ሐብት መሪነት ጨ
በጠች::

በካፒታሊዝም ያልተስተካከለ ዕድገትና ልማት ምክንያት
በኢምፔሪያሊስት መንግሥታት መካከል የሚገኘው የሃይሎች መዛመዱ
ወይም መዋጀት ያለማቋረጥ የለዋወጣል:: ይህም ሁኔታ በካፒታ
ሊስቶች ሃይሎች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች አሻክሮ በማባባስ
ጦርነቶች ያስከትላል:: የኢምፔሪያሊስቶች ጦርነቶች ዐይነተኛው
መንስኤያቸው ምጣኔ ሐብት ነው:: በዚህ አኳኋን የኢምፔሪያሊስ
ት መዝባሪያች የተከፋፈለውን ዓለም በጦር ሐይል እንደገና በአ
ዲስ መልክ ለመከፋፈል ይሞክራሉ:: ባለንበት ምዕተ ዓመት ብዙ
ጦርነቶች ተካሂደዋል:: የአብዮትና የነፃነት መውጣት እንቅስቃ
ሴዎች በኢምፔሪያሊዝም ቢዳፈን ኖሯል:: በዘመነ ኢምፔሪያሊዝም
ተቀጽላነት፣ ያለአግባብ መበልጸግን፣ የዲሞክራሲ መጨቆን፣ የብ
ሔራዊ ጭቆና መክረር እንደነበልባል የሚንቀለቀል ዘረኝነት መስ
ፋፋት ይገናል::

ይህን የታሪክ ማገናዘቢያ ከአገራችን ሁኔታ አንፃር
ብዙ ቁም ነገሮችን ይጠቁመናል:: ሶቪየት ህብረት ለአገራችን
ዋና ጠላትነቷን የምንለካው የአገራችንን ነፃነት በመዳፈሯ፣ የ



አገራችንን ኢኮኖሚ ዕድገት ስለምትቁጪ ፀረ ዲሞክራቲክ አገዛዝ
ፖሊሲን ስለምትከተል፣ በአገራችንም በመጫወት ላይ ያለቻው አደ
ገኛ ፖሊሲ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአንድነት አገር አቀፍ ትግል
ማድረግ እንዳለባቸው ያስገነዝበናል:: የተማሪው ድርጅት ንቅና
ቄም አንድነት ከምንጊዜም በበለጠ የሚሻው የዛሬዎቹ በአገራችን
ላይ ተንሰራፍተው የሚገኙት ጣምራ ጠላቶች ቀራኒያቸው ከኢትዮጵ
ያ ሕዝቦች ጋር በመሆኑና ፀረ ዲሞክራቲክ ሃይል የነገሰበት ወ
ቅት በመሆኑ ነው::

የወታደሩ መንግሥት ከስልጣን ኮርቻ ሳለመውረዱም ትምባ
ገነናዊ አገዛዙን በደንብ የሚቀጥልበትን መንገድ ቢሮክራቲካዊ
አውታሮቹ እየደገፉት ነው:: ስለቢሮክራሲ ስናወሳ ቢሮክራሲ የ
ሚለው ቃል የሚያመለክተው አንድም አስተዳደራዊ መስሪያ ቤቶችን
ድርጅቶችን በአጠቃላይ ሲሆን አንድም የነዚህን የአሰራር ዘይቤ
ነው:: ቢሮክራሲ ባጠቃላይ የመጨቆኛ ሥርዓትን ማስጠበቂያ መ
ሣሪያ ነው:: ስለሆነም በህዝቦች ፍላጐትና ዕምነት ላይ የተመ
ሰረተ ባለመሆኑ የጨቋኞች መንበራሪያ፣ የሥልጣን መባለጊያ፣ ሰ
ፊው የሚገለገልበት ሳይሆን ፍትህና ርትዕን የሚያጣበት ከባድ
ጭነት ነው:: በአሁኑ በአገራችን ሁኔታ የወታደር አምባገነናዊ
አገዛዝ በብዙ ምስያዎች እየተተከሉ ነው:: በቅርቡም "የሰርቶ
አደር ፓርቲ አደራጅ" በሚል ስያሜ የተያዘው ሸር ጉዱ በአገር
አቀፍ ደረጃ ሕዝቡን እጅ ከወርች በማሰር በሕዝቦች ዲሞክራሲ
መብት ላይ የሚጋልብ ለመሆኑ በይፋ እየታየ ነው::

በመጨረሻም ተግባራችን ምን መሆን አለበት የሚለውን
ለመመለስ እንሞክራለን፣

1. የድርጅታችን መድረክ ፀረ ፊውዳል፣ ፀረ ቢሮክራቲክ ካፒ
ታሊዝም ፀረ ኢምፔሪያሊዝም በመሆኑ እነዚህ ዋና የኢትዮ
ጵያ ሕዝቦች ጠላቶች በመሆናቸው ድርጅታችን ሃይሉን በሚ
ገባ አሰባስቦ በማጋለጥ፣ በቀስቃሽ በሌላም ዘዴ እነዚህ
ጠላቶች በምን ሁኔታ በአገራችን ሰፍነው እንደሚገኙ ማወ

ቅ ማሳወቅ ይኖርበታል::

2. ንቅናቄያችን በኢትዮጵያ ሕዝቦች መሠረታዊ ጠላቶች በሆኑት ላይ በቂ ጥናቶችን እያደረገ ሰፊ ዲሞክራቲክ ንቅናቄ ግንባር እንዲፈጠር መታገል ይኖርበታል::

3. የኢትዮጵያ ሕዝቦችም የጋራ ጠላት ያላቸው መሆኑንና፣ ብርቱ የሆነ ጠላታቸውን ለማሸነፍ አማራጩ ጎዳና የጭቁኖች እጅ ለእጅ በትክክለኛ ዲሞክራቲካዊ ግንባር መያያዝ በወቅቱ መፈጸም የሚገባው ጥያቄ መሆኑን ማስገንዘብ፣

4. የደርጉን ኢዲሞክራሲያዊ አምባገነናዊ አገዛዝ፣ ሸቨኒስት ፖሊሲ፣ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ዕለታዊ ኑሮ ላይ የሚያደርሰውን ግፍና በደል ማጋለጥ፣

5. ደርግ የአገራችንን ነፃነት አሳልፎ ለውጪ ሃይል የሰጠ በመሆኑ፣ ይህን ወጣቱ፣ ዲሞክራቱ፣ አገር ወዳዱ መገንዘብ ብቻ ሳይሆን መታገል የርቀቱ ግዴታ መሆኑን በመረዳት የሚጠበቅብንን ድርሻ ማበርከት፣

6. በአገራችን ያሉት የሕዝቦች ንቅናቄ በተለይም የብሔሮችን ትግል ዲሞክራቲክ ንቅናቄ ጎኑን በመደገፍ የሚደረገው የትግል ትብብር እንዱ ጎሮሽ ብቻ መሆን የለበትም:: ይህም ማለት ለዲሞክራሲ በሚደረገው ትግል አገር አቀፍ የነፃነት አቅኚ ትግሎችንም ጎዳና የሚዘጋና የጭቁን ብሔሮችን ርስ በርስ ጥላቻ የሚያፋፍም መሆን የለበትም:: ስለሆነም ለዲሞክራቲክ ንቅናቄዎች የሚሰጠው ድጋፍ በአንፃሩም ያሉትን የደካም ጎኖችን ለማጋለጥ ከፍተኛ ጥረት መደረግ ይኖርበታል::

7. በአጠቃላይ በአፍሪካ ምድር በስደት ላይ ያሉትን ኢትዮጵያውያኖች አስከፊ የኑሮ ስቃይ ለዓለም አቀፍ ሰብአዊ ድርጅቶች በማስተዋወቅ ርዳታ የሚደረግበትን ዘዴ መሻት፣

8. ለስደተኞች በአውሮፖ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያኖች፣ ከሌሎችም ለጋሾች ርዳታ የሚገኝበትን ዘዴ በማጥናት የቁሳቁስና የገንዘብ ርዳታዎችን በመሰብሰብ ርዳታውን ማድረስ::



## የየካቲቱ ሕዝባዊ ንቅናቄ ቢታወስ

የኢትዮጵያ ህዝቦች ብዙ አኩሪ ትግሎች አሏቸው:: ለነፃነት ብዙ ተጋድሎ ተደርጓል:: የዘባን አገዛዝ በመቃወም በዱር በገደሉ ሕዝቦች አምፀው ታግለዋል:: ግን የየካቲቱን ሕዝባዊ አብዮት ልዩ የሚያደርገው ነገር ቢኖር የኢትዮጵያ ሕዝቦች አገር አቀፍ ንቅናቄ ያደረጉበትና የህዝቦች ሃይልና አንድነት አድሀሪ ሃይሎችን ለመገርሰስ አማራጭ የማይገኝለት መሆኑን በግልጽ በማሳየቱ ነው::

ልክ የዛሬ 7 ዓመት የኢትዮጵያ ህዝቦች በአንድነት፣ ከአድሀሪው አገዛዝ ጋር የተፋጠጡበት፣ የህዝቦች ወዳጅና ጠላት ሚናቸውን ለይተው በትግል የተፋለሙበት ወቅት ነው:: የየካቲቱ አብዮታዊ ማዕበል ከፊቱ የተጋረጡትን ብዙ መሰናክሎች እየተጋፈጠ የገዥውን መደብ በፍርሃት፣ በስጋት እንዲዋጥና ለሕዝቦች ጥያቄዎች እንዲንበረከክ አድርጓል:: የየካቲቱ ሕዝባዊ ቁጣ፣ ሰፊው ሕዝብ የሰነዘውን በትር አቅጣጫ ለመለወጥ ብዙ የማወናበጃ ዘዴዎች ተሞክረዋል:: ሕዝቡ ነፃነት ሲል፣ አጭበርባሪዎች የነፃነትን ፍች ይለውጡበታል፣ ሕዝቡ መሬት ለአራሹ ሲል፣ አጭበርባሪዎች የመንግሥት መሬት ማደል ነው እያሉ፣ ሕዝቡ የሚጠይቃቸውን የመብትና የነፃነት ጥያቄዎች ለማጣመም ብዙ ሴራዎች ተደርገዋል:: ሆኖም ሲፈርስ የተቃረበን ቤት ከመሰረቱ አፍርሰው ካልሰሩት ዋስትና የለውምና በሕዝብ ቁጣ ፍርከስከሱ የወጣው ሥርዓት ምንም ምንም ዓይነት ጥገና ሊያድነው አልቻለም:: በየካቲት የሕዝቡን እንቅስቃሴ በመከተል ልዩ ልዩ አመለካከቶች ኢትዮጵያ ወዴት? የሚለውን መልስ ለመስጠት በመገናኛ መሳሪያዎች ቢረጩ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣ ሁሉ ላይ ብዙ ሽሚያ ነበር::

በ1974 ዓ.ም የካቲት የሕዝቦችን ሰፊ ንቅናቄ ያስተሳሰረው የዲሞክራሲ ጥያቄ ነበር:: መሬት ለአራሹ የገበሬው ዲሞክራሲያዊ ጥያቄ ነበር፣ የመደራጀት መብቱ ለዘመናት የተገ

ፈፊው የሠራተኛው ክፍል ያለአንዳች ገደብ መደራጀት ውይይት ማድረግ የዲሞክራሲ ጥያቄ ነበር፤ አገራችንን ከሃያል መንግሥታት ቁጥጥር ነፃ አድርጎ በራሷ ሕዝቦች የጋራ ዕምነት ላይ ያረፈ ፖሊሲን በመንደፍ አገራችን ከሰላም ወዳዱ ህዝቦች ጐን ለመሰለፍ የሚያስችለንን ጐዳና እንድትጠብቅ ማድረጉ ህዝባዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያን መመኘት ነበር፤ የብሔረሰቦች እኩልነት እንዲከበር የተነሳው የህዝብ ወገን የዲሞክራሲ ጥያቄ ስሳለው ነበር፤ ሌሎችም የህብረተሰቡ ጭቁን ክፍሎች ያቀረቡት ጥያቄ ሁሉ ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያን የመፍጠሩ ጥያቄ ላይ ያተኮረ ነበር:: በተጨማሪም የእንቅስቃሴው ልዩ ባህሪ በየጊዜው አብዮታዊ መንፈስን እየተሳበሰ መሄዱ ነው:: በአጭሩም ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል የተፋፋመበት ወቅት ነበር:::

በየካቲት ሕዝባዊ ንቅናቄ ገበሬው፤ ሠራተኛው፤ ንዑስ ከበርቴው፤ ወጣቱ፤ አገር ወዳድ ሁሉ እጅ ለእጅ በመያያዝ በጋራ ጠላቶቻቸው ላይ የተባበረ ክንዳቸውን በማንሳት፤ ገንባራቸውን ሳያጥፉ በመታገላቸው ሳአጭር ጊዜም ቢሆን ባየካቲቱ የሕዝቦች ንቅናቄ ብዙ ሕዝባዊ ፀባይ ያላቸው የትግሉን ደረጃና ባህሪ የሚያጠናክሩ ዘሮች ተዘርተው፤ በዙያቸውም አበባቸው መታየት ቢጀምር የህዝባችንን የዲሞክራሲ መብት በሚነፍግ ሐይል ተነጥቀዋል በተለይም ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያን ለመፍጠር ጊዜን፤ ዘዴን፤ የመረረ ትግልን በሚጠይቅበት ወቅት ለተገፋው ሕዝብ በተገቢ መንገድ አርአያ ለመሆን የሚችል ተወካይ ድርጅት ባለመኖሩ የየካቲቱ ሕዝባዊ ንቅናቄ በአጭሩ ተቀጭቷል:: በእርግጥም የየካቲቱ ሕዝባዊ ንቅናቄ ከዘራቸው የፖለቲካ ዘሮች መካከል ሕዝቡ በትግሉ የተወሰኑ ድሎችንም ተጎናፅፏል:: እነዚህም ድሎች ተብለው በአገራችን የሚነገሩት ነፃ ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያን ለመገንባት በሚያስችል ሁኔታ ባለመያዛቸው አገራችን አሁን ያለችበትን ሁኔታ እንድትደርስ ምክንያት ሆኗል::

በሌላውም በኩል የየካቲቱ ሕዝባዊ ንቅናቄ ለህብረተ



ሰባችን ተራማጅ ክፍሎች ያቀረቡት ጥያቄዎች ቢኖሩ የትግሉ ዓላማ ወይም ግብ ምንድነው? የትግሉ ወዳጆች ወይም ተባባሪ ሐይሎች እነማን ናቸው? ጠላቶችስ? የትግሉ ጠቅላላ ባህሪ ምንድነው? የወደፊት አቀጣጫውስ? እነዚህን ጥያቄዎች ርዕዮተአለማዊ አመለካከት በመስጠት በኢትዮጵያ ሕዝቦች የትግል ማዕበል ውስጥ ከተማገዱት ሃይሎች ውስጥ ኢሕአፖም ይገኝበታል:: የየካቲቱ ሕዝባዊ ንቅናቄ አቀጣጫውም፤ ደረጃውም መሣሪያ ባነገበ ሃይል ቁጥጥር ስር ከዋለበት ጊዜ አንስቶ በኢሕአፖ ላይ ከገጠው ክፍል በተሰነዘረው የዕልቂት አዋጅ ኢትዮጵያ አገራችን ብዙ የጭቁን ህብረተሰብ አካሎችን እንዲታጣ ምክንያት ሆኗል:: በጠቅላላው ንቅናቄው የፈጠራቸው ድርጅቶችም ለአብዮቱ ትክክለኛ አመራር ባለመጠበጣቸው ያስከተሉት ዕልቂት በአሁኑ ትውልድ የሚዘነጋ አይደለም:: ይህም በየካቲቱ ህዝባዊ ንቅናቄ የማይናቅ ሚና ከተጫወቱ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ሠራተኛው፤ ገበሬው፤ ወጣቱ ሌሎችም ተፈጥሮ ከነበረው ሁኔታ ለማዳን በባዕድ አገር እንዲሰደዱ ተጨማሪ ምክንያት ነበር::

የካቲት ትውስ የሚለን ከብዙ ሁኔታዎች ጋር ነው:: የኢትዮጵያ ህዝቦች የተዋደቁበት፤ ከአገራቸው የተሰደዱበት፤ በወህኒ የታጐሩበት ጥያቄ ምን ነበር? አሁንስ ምን መልክ ይዟል? ለወደፊቱስ እንደሕብረተሰቡ አካልነታችን ምን ድርሻ ይጠበቅብናል የሚለውን ለመመለስ በምናስብበት ወቅት የካቲትን እናወሳዋለን:: ለውጥ ፈላጊ ሃይል ሁሉ የለውጥ መምጫ ጎዳናን በዘፈቀደ አይመለከተውም:: ስለሆነም በየካቲት የፈነዳው የሕዝቦች ንቅናቄ በጉዞው ላይ ከተደናቀፈ ወዲህ በአገራችን ብዙ በደሎች እየተፈጸሙ ነው:: 'በኢትዮጵያ ሶሻሊዝም' ስም የህዝቦች የዲሞክራሲ መብት እየተረገጠ ነው፤ 'በኢትዮጵያ ሶሻሊዝም' ስም በኢትዮጵያ ከአድሀሪ የህግ ጥርቅም ነፃ የሆነ ድርጅት ማቋቋም በህግ የተከለከለ ነው፤ እንዲያ በየካቲቱ የትግል ማዕበል አንዱ ሆኖ የተነሳው የኢትዮጵያ ህዝብ በአሁኑ ወቅት የትግል መበ

ታትን ደርሶበታል:: በግራው ኃይል በኩል ያለው መበታተን የበለጠ ገኖ ይታያል:: በሌላው አንፃር የኢትዮጵያ ህዝቦችን መሠረታዊ የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመሰብሰብ ነፃነቶችን የገፈፈው የወታደሩ መንግሥት ከሶቭየት ህብረት ጋር በመሳጠፍ ብዙ ኢሰብአዊ ድርጊቶችን እየፈጸመ ነው::

ከየካቲት ወዲህ አገራችን የት ደርሻለች? የሚለው ጥያቄ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ዘንድ የሚጉላላ ሐሳብ ነው:: ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ማድረግ ማለት የፊውዳሊዝምን ጠንቆች መደምሰስ በምትኩ ለህዝቦች የሚበጅ መትከል ማለት ነው፣ ፀረ ኢምፔሪያሊስት ትግል ማድረግ ማለት የአገርን ነፃ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የሶሻል ሀይያችን የዕድገት ጉዳዮችን በህዝቦች ብልጽግናና ሥልጣኔን በሚያጎናጽፍ ጎዳና ማነፅ ማለት ነው:: የኢትዮጵያ ህዝቦች ይህ ዓላማቸው በየካቲት አገር አቀፍ ትግል ተጠንስሶ ነበር፣ ዛሬ ፈሩን ለቆ ኢዲሞክራሲ አገዛዝ ሰፍኗል:: የሕዝቦች ድምጽ፣ የሕዝቦች ትግል ተከደ፣ ተረገጠ የወታደር አምባገነን አገዛዝ የበላይነቱን ጨብጧል::

ይህ የየካቲት ንቅናቄ በትክክለኛ ይዘቱ፣ በተነሳበት የተጋደሉ ጥያቄዎች፣ ከተነሱት የሕዝብ መፈክሮች አንፃር የሕዝቦች በዓል ነው:: የየካቲትን ንቅናቄ አጭበርባሪዎች ካላጣመሙት በስተቀር ነፃና ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያን ለሚሹ ሁሉ ትልቅ በዓላቸው ነው:: በዓልነቱ የኢትዮጵያ ህዝቦች የየካቲቱን ትግላቸውን ጨብጠዋል ከሚለው አንፃር አይደለም፣ በዓልነቱ የአገራችን ህልውና ለውጪ ሃይል መሸጡን በመቀበል አይደለም፣ በዓልነቱ ጨቋኞች በአገራችን ስለተደላደሉ አይደለም፣ በዓልነቱ በጤራዊ ስሜት ላጡት ገሸያች ማቀገሻ አይደለም:: በርግጥ በዓልነቱ የየካቲት የተገለደወል፣ የትግል ወኔና መንፈስ በመከተል የጭቁኖች ግንባር ዲሞክራቲክ ኢትዮጵያን ለመፍጠር በሚደረገው ትግል ከፍተኛ ጥሪ ስላለበትና የየካቲትን አርማ ይዘው ለታገሉት ለወደፊትም ለሚታገሉት ትልቅ መታሰቢያ በመሆኑ ነው:: መታሰቢያነቱ



ለጭቁኖች ትግል ከፍተኛ ትምህርት በመስጠት ያለፈ ቢሆንም ጭቁኖች ደግመው ደጋግመው የካቲትን የሚያስታውሱት የየካቲት ኢላማዎች አሁን መልካቸውን ለውጠው መቀመጣቸው፣ ሌላ ትግል የሚጠይቅ በመሆኑ ነው:: ይህም በአጭሩ፣

1. የወታደሩ መንግሥት ፀረ ዲሞክራቲክ አገዛዝን መታገል፣
2. የአገራችንን ነፃ ህልውና አሳልፎ በሰጠው የወታደሩ መንግሥት ላይ የኢትዮጵያ ህዝቦች ከመቸውም ጊዜ በበለጠ በመተባበር እንዲታገሉት የወቅቱ ጥያቄ በመሆኑ፣
3. በአገራችን የዲሞክራሲ ጭላንጭል የተዳፈነበት በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ለዚህ መሠረታዊ ነፃነታቸው መታገል እንደሚኖርባቸው፣
4. የብሔረሰቦችን እኩልነት በገቢር ለማዋል በጭብጥ ዋና መንደርደሪያ ዲሞክራሲን በአገራችን ማስፈን በመሆኑ፣ ለዚሁ ቁልፍ ጥያቄ የትግሉ አማራጭ የብሔረሰቦች አንድነት በዋና ጠላት ላይ ማተኮር የሚኖርበት መሆኑን በመገንዘብ ነው፣

የሕዝቡ ትግል በማይነጠቀበት አኳኋን ዳግማዊ የካቲት በአገሪቷ የነገሰውን አድሀሪ ሃይል ለማንበርከክ ችሎታ ይኖረዋል ብለን እናምናለን:: ስለሆነም በአውሮፓ የኢት. ተማ. ማህበር /ዓ.ዓ. የኢ.ተ.ፌ.አባል/ የካቲትን ያስታውሰዋል:: ቀ/ማኅበራትም ምሽቶችንም ሁነ ሴሚናሮችን በማዘጋጀት 7 /ሰባተኛውን/ ዓመት የየካቲትን ንቅናቄ ያከብሩታል::

የየካቲት ትግል ይለምልም!

## ON THE COMMEMORATION OF THE FEBRUARY MASS UPSURGE

Eversince the emergence of the present day multi-national state of Ethiopia, our country has never been independent in the true sense of the word. Even though our courageous people have fought back direct aggressors and colonizers, the country has suffered under the neo-colonizers, particularlly the American-Imperialism. The spinless feudal aristocracy under the leadership of Haile Selassie made many political, economical, cultural and military pacts which reduced the country to a vassal state and the people to second class citzens in their own country. As a result of this national betrayal, the Ethiopian people have been kept under the bondage of feudalism, beuracratic capitalism and imperialism.

This intolerable, backward system led the Ethiopian people to the battle ground inorder to fight it back. The year 1974 was such a period, a period of mass upsurge. It was also a turning point in the history of the Ethiopian toiling masses, on the ground that for the first time different stratas, classes and nationalities rose hand in hand to express their griviancies and bitterness against the system, it was a time when the people become concious of their mighty power, it was a period when the oppressed people experienced the significance of the inter-class, inter-nationalities solidarity, above all it was also a period when our people recognized the lack of class organization i.e class party. As Ethiopia is no different than any other backward African countries, the only organized social power was the military which managed to usurpe the the state power easily. After usurping the state power, even though it has accomplished some reforms on the bases of the relentless struggle of the toiling masses, it has proved its incapablity of fullfilling the fundamental political, economical and social demands of our society. On the contrary it has aggravated the situation with only high emphasis of strengthning its political power.



The split among the left movement has also favoured the undemocratic military regime to stabilize itself, through the unholly alliance with the Soviet Union, which was keeping a bulged and prayed eye on the Ethiopian revolution.

The junta opened the door wide and the Soviet Social imperialists tighened their grips to help the "Ethiopian socialism and revolution". Thousands of the Cuban mercenary troops and hundreds of East European military "advisors" were stationed in Ethiopia and the Soviet Union amassed a huge quantity of military "aids" to the junta. The junta signed a twenty years pact with the Soviet Union which further affirms the neo- colonial status of Ethiopia to the Social Imperialists. This pact legalises the soviet control over the life of Ethiopia and its fate.

The country's situation is deteriorating in every passing moment. Starvation swarms unprecedently the country and it's offering untold number of deathes throughout the country. The junta and the social imperialists are contending and colliding the oppressed nationalities for their own cursed ends. Opressed nationalities and patriotic masses are daily bombarded and their villages burned to ashes. Thousands of Ethiopians fled their country and are now refugees in neighbouring countries and all over the world. The refugees conditions in the Sudan, Somalia, and Djibouti is so appalling that even the international human-right organizations are publicising about it. The situation for the Ethiopians at hom is inexplicably deteriorating.

Would it be far from the truth if we say that the Ethiopian masses are disillusioned and their struggle is uncoordinated for the moment? The Ethiopian masses face this reality and they are striving upto it. The Ethiopian masses have the confidence inthemselves, no matter how their struggle is complex that all of them irrespective of religion, sex, nationalities etc. would make a revolution like the february once again and again. Their daily experience is teaching them that their joint struggle to overthrow their

common enemies i.e the junta and the soviet social imperialism will embark them to freedom. A common commanding staff of struggle until the victory over the junta and the soviet social-imperialism is the only guarantee that our masses can be free and their genuine aspiration cemented together forever. If their struggle is channeled to this goal, the rebirth of the New February Revolution is not far away from our masses.

LONG LIVE THE FEBRUARY REVOLUTION!

THE ETHIOPIAN MASSES SHALL BE FREE!

DOWN WITH THE MILITARY JUNTA!

DOWN WITH THE SOVIET SOCIAL-IMPERIALISM!